

ካህናቱ እርሻውን ለማረስ ሞፈር ቀንበር ይዘው ሲዘጋጁ

ዋጋው ሃምሳ ሳንቲም

# ትንሣኤ



የጥምቀት በዓል አከባበር

ቁጥር ፴፱ ጥር ፲፱፻፸፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ስሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ፡፡ »

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ

# ማ ው ጫ

## ኦርእስት ፣ ገጽ


ደብዳቤዎች ............ ፩
መልካም እርምጃ ............ ፪
ቤተ ክርስቲያናችን ዳግመኛ ኢታጠምቅም ............ ፬
እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ............ ፮
ሴቶች በማህበራዊ ኑሮ ............ ፯
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፰
የእግዚአብሔር መገለጥ ............ ፲
የጎለቃ ሺ.ዋጋህ አሰማህኝ አጭር የሕይወት ታሪክ ............ ፲፩
አዲስ ምዕራፍ ............ ፲፪
የግብርና በረከት ............ ፲፬
ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብ ............ ፲፮
እርጅና ............ ፲፯
በትምህርት አሳብ ልመና ............ ፲፰
የማሰዝ ትም ... ............ ፳፩
ተሳላፊ ሀሽታ ............ ፳፪
............ ፳፫


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ መንፈሳዊ ሥራችሁ የተቃና ይሆን ዘንድ እመኛለሁ ፤ በድርጅታችሁ አንዳንድ የጠና ምክንያት ያጋጠማቸው ሰዎች በሚያቀርቡላችሁ ጥያቄ መሠረት መልስ በመስጠት ችግራቸውን እንደምታቃልሉ አውቃለሁ።

አሁንም በሃይማኖት የነበረው ሥርዓት ያለ አገባብ ሲፋለስ ትክክለኛውን መልክ በማስያዝ መልስ የሚሰጥበት መሆኑንም እረዳለሁ ለሚቀርቡላችሁ ችግሮች በአስፈላጊው መንገድ መልስ በመስጠት ከችግር ደስታን እንዲያተርፉ በማድረግ ሰዎችን ረድታችኋል ፡፡

አሁን እኔ የገጠመኝን ችግር ከማቅረቤ በፊት ራሴን ከነአድራሻዬ አስታውቃለሁ ፡- ስሜ አቶ ሐሰን ሑሴን ፣ አድራሻዬከ. 16ቀበሌ 04 የቤት ቁ.555 ሃይማኖቴም የእስልምናሃይማኖት ተከታይ ነኝ ጥያቄየም ፩ኛ በማንኛውም የሃይማኖት ሥርዐት አባቱና እናቱ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ልጃቸው የክርስትና ሃይማኖት ያልተቀበለ ወይም ያልተጠመቀ ዕድሜው ገና ፲፩ ዓመት የሆነው የሌላውን የክርስቲያን ልጅ ክርስትና ሊያነሣ ይቻላልን ?

፪ኛ/ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ከእስላም መስጊድ ገብቶ መስገድ ይገባዋልን ? በአንጻሩም የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነ ወደ ቤተ ክርስቲ፡ያን ገብቶ ሊሰግድ ይችላልን ?

፫ኛ/ እስልምናና ክርስትና የሚለያዩበት በምንና በምን ምክንያት እንደሆነ ይብራራልኝ ፡፡

፬ኛ/ ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሆነኝ የክርስትና እምነት ተከታይ ያልሆነው የክርስቲያኑን ልጅ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም. በመንበረ ፀባዖት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል ክርስትና ሲያነሣ በማየቴ ነው ፡፡

ከዚህ ላይ ናስር ሐሰን የስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን የክርስቲያኑን የአቶ በፈቃዱን ልጅ ክርስትና ሲያነሣ ካህኑ ክርስትና አንሺውን ክርስቲያን መሆኑንና መጠመቁን እንዴት አልጠየቁም ሊጠይቁስ አይገባምን ?

በጣም የሚደንቀው የክርስቲያኑ ልጅ በእስላሙ መነሣቱ ነው ይህ ሲደንቀኝ የዚሁ የክርስትና አንሺ ልጅ እናቱ ወ/ሮ ታደለች ወ/ማርያም ከእኔ ከእስላሙ ባለቤታቸው ጋር ለ፴ ዓመታት በባልና ሚስትነት ሲኖሩ ፲ ልጆችን የወለዱ ሲሆኑ ይህንኑ የክርስትና እምነት ገና ያልተቀበለውን ክርስትና እንዲነሣ ሲያደርጉ ለእኔ አለመግለጻቸው ትክክል ነውን ? የጋብቻው መፍረስስ በሃይማኖት ሥርዓት ምን መፍትሔ ይፈለግለታል ? ለጥያቄዎቼ መልስ ለማግኘት እጠባበቃለሁ ፡፡

አቶ ሐሰን ሁሴን
አዲስ አበባ

አቶ ሐሰን ሁሴን በመጽሔታችን እየታተሙ የሚወጡትን አንዳንድ ሕብረተሰብ ነክ ትምህርቶችን በመከታተል ተገቢውን መልስ አገኛለሁ በማለት ስለአቀረቡልን ጥያቄ እናመሰግናለን ፣ ወደፊትም መጽሔታችንን እየተከታተሉ በማንበብ ኅብረተሰብ ነክ የሆኑ ጥያቄዎችን ቢያቀርቡልን መልስ ለመስጠት ዝግጅዎች መሆናችን እናረጋግጥለዎታለን ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ላቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ፤

፩ኛ/ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት መሠረት የክርስትና እምነት የሌለው ሰው የክርስቲያኑን ሰው ልጅ ክርስትና እንዲያነሣ አይፈቀድለትም በመሠረቱ የክርስትና አባት ሃይማኖት እያስተማረ ልጁን ለማሳደግ ቃልኪዳን የመግባት ግዴታ አለበት ፤ በተጨማሪም ክርስትና በሚነሣበት ጊዜ የሕፃኑን አውራ ጣት ይዞ የሃይማኖት ጸሎትን የመድገም ግዴታ ያለበት የክርስትና አባቱ ነው ፤ ምን አልባት የሃይማኖት ጸሎትን ለመድገም ቢያቅተው ዲያቆኑ ወይም ቄሱ ይደግምለት ይሆናል ፡፡ ይህም ካለመማር የተነሣ የሚፈጸም እንጂ ትክክለኛ ሥርዓት ነው ለማለት አይደለም ፤ ስለዚህ ያልተጠመቀ ሰው እንኳን የክርስቲያኑን ልጅ ክርስትና ሊያነሣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት እንደሌለበት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናችን ይከለክላል ፡፡

፪ኛ/ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆነ ሰው ወደ እስላም መስጊድ ገብቶ መስገድ ተገቢ አለመሆኑን በቤተ ክርስቲያናችን ሕግ በጥብቅ የተከለከለ ነው ፡፡

፫ኛ/ የእስልምናና የክርስትና እምነት የሚለያዩበት ብዙ መንገዶች ሲኖሩ ከብዙዎቹ ዋነኛው ጥምቀት ነው ፡፡

፬ኛ/ ጠያቂው እንደገለጹት ክርስትና ለማንሣት የቀረበውን ሰው ሃይማኖት አጥማቂው ካህን አለመጠየቃቸው ሊያበቅ የማይችል ዓቢይ ስሕተት ነው ቢሆንም ካህኑ ለምን ሳይጠይቁ እንደቀሩ ቢጠየቁ ተመዝግቦ የቀረበልንን ማጥመቅ እንጂ የክርስትና አባቱን ስምና የወላጆቹን ስም የሚመዘግበው ሌላ ክፍል ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል ክርስትና የሚነሡትንና የሚያሥነሡትን የሚመዘግበውንም ክፍል ብንጠይቅ አንዳንድ ሰዎችየመጠሪያ ስማቸውሐሰንሑሴንናስርወዘተነው ይህስምየእስልምና እምነት ተከታይ ስም ነው እንዴት በዚህ ስም ልትጠሩ ቻላችሁ? ስንላቸው የክርስትና እምነትን ከመቀበላችን በፊት ስንጠራበት የቆየ በመሆኑ አሁን ለመለወጥ ብዙ ችግር ስለገጠመን ነው የሚል መልስስለሚሰጡን በስምበኩልያለውንጥያቄችል ልንለው ችለናል ሲል መልስ ሰጥቶናል ፡፡

አጥማቂው ካህንም ሆነ መዝጋቢው ክፍል በንዝህላልነት ባደረጉት ስሕተት ከተጠያቂነት የሚያመልጡ አይመስለንም ይህ ያለፈው ስሕተት ትምህርት ሁኖአቸው ለወደፊት እንዲጠነቀቁ በዚህ አጋጣሚ ለመላው አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ መልእክታችን እናስተላልፋለን ፡፡ ስለወይዘሮ ታደለች አቶ ሑሴን ያሉት እርግጥ ከሆነ ታላቅ ስሕተት ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

## መልካም እርምጃ

ለእርምጃ ቅድምናው ውሳኔ ነው ፤ ከውሳኔም ውይይት ይቀድማል ፤ ጉዳዩ ሁሉ በውይይት ይቀየሳል ፤ በውሳኔ ይጸድቅና በእርምጃ ይፈጸማል ።

እርምጃ የማይከተለው ውሳኔ ግን ማሠሪያ እንደሌለው ፍልጥ የተበታተነ ሁኖ ከመቅረት በስተቀር የሚያበረክተው ጥቅም አይኖርም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን በመወያየት በየጊዜው ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ለአብያተ ክርስቲያናት ያስተላልፋል ከሚያስተ ላልፋቸውም በርከት ያሉ ውሳኔዎች ጥቂቶቹ በሥራ ላይ ሲውሉ የቀሩት የጀሮ ቀለቦች ሆነው ሳይፈጸሙ ይቀ ራሉ ፤

ይህም ሊሆን የሚችለው ቀደም ብሎ ለሚተላለፉት ውሳኔዎች አስፈጻሚ ክፍል ባለመኖሩ ፤ ወይም ጠበቅ ያለ እርምጃ ስለማይወሰድባቸው ነው ። ይህንን በመመልከት ቅዱስ ሲኖዶስ ጳጉሜን 1 ቀን 1974 ዓ. ም. ባደረገው ስብሰባ አንድ ተፈላጊ የሆነ እርምጃ ወስዷል ፤ እርምጃውም እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ ስዕል መስቀል ይዘው በየመንገዱና በየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዲሁም ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ተነሥተው ወደሌላው ሰበካ እየዞሩ የሚለምኑ ፤

2ኛ/ ሱቲ አንጥፈው ደንጊያ በጀርባቸው በትከሻቸው ተሸክመው ፤ ብረት ታጥቀው ስለስዕለት አትለ ፉን ፤ ስጡን ፤ እያሉ በመማጠን ቤተ ክርስቲያን ተሳላሚውን ሕዝብ ግራ የሚያጋቡ ፤

3ኛ/ በዓመትና በወር በዓላት ፤ እንዲሁም በዕለተ ሰንበት በቤተ ክርስቲያን ቅጽር አካባቢ ሸቀጣ ሸቀጦችን ደርድረው የሚሸጡ ፤ የሚለውጡ ሁሉ እንዲከለከሉ ትእዛዝ ለመላው አብያተ ክርስቲያናት ሲያስ ተላልፍ ፤ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚሸጠውና የሚለወጠው ሸቀጣሸቀጥ ቅመማ ቅመም ከቤተ ክርስቲያና ችን ባህልና ሥነ ሥርዓት ውጭና አስነዋሪ ተግባር መሆኑን አሳስቧል ።

የቅዱስ ሲኖዶስ እርምጃ አስፈላጊና ወቅታዊ በመሆኑ የአድባራት አለቆች ፤ የገዳማት አበምኔቶች፣ ካህናት ፤ የሰበካ ጉባኤ አባላትና ምእመናን በመተባበር ውሳኔውን የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው ።

ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ፤ የስግደት ፤ የአስተብርኮት ፤ የፍቅር ፤ የርኅራኄ ፤ የሰላም ፤ ወዘተ ቦታ ስት ሆን የሸቀጣሸቀጦች ማጣሪያ የሥራ ጠሎች ማታለያ ሆና መገኘት የለባትም ፤ ሕዝበ ክርስቲያኖቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ጸጥታን ይፈልጋሉ እንጂ ፤ ከገበያ ሊገዟቸው የሚችሏቸው ሸቀጣሸቀጦች በየመንገዳቸው ተደቅነው እንዲቆዩአቸው አይሹም ፤ ስዕል መስቀል ይዘው ሱቲ ዘርግተው የሳንቲም ድቃቂ የልብስ እላቂ እያሉ የሚያዋክቡ ሰዎችም በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቋቸው አይፈልጉም ።

ነገር ግን ሸቀጣሸቀጦች በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ተደርድረው የሚሸጡና የሚለወጡ ከሆኑ ምእመናኑ ከተመለከቷቸው ዕቃዎች ገዝቶ የመመለስ ፍላጐት ያድርባቸዋል ፤ ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ብለው አስበው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ ላላሰቡት ዕቃ አውለው ወደ ቤታቸው ከመመለስ ይደርሳሉ ፤ ይህም ጉዳቱ የቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ወደቤተ ክርስቲያን የሚመጡትንም ክርስቲያኖች ክብረ ነፍስ የሚያሳጣ ነው ።

ለቤተ ክርስቲያን ዕጣን ፤ ጧፍ ዘቢብ ወዘተ ገዝቶ በመስጠት ፈንታ በድንገተኛ አሳብ ተሸንፎ ያላሰ ቡትን ዕቃ ገዝቶ ይዞ ወደ ቤት መመለስ "እጸድቅ ብሎ ኩነኔ" እንደሚባለው የአባቶች ምሳሌ ነው ።

ለሁሉም ቦታና ጊዜ ስላለው ለጊዜውና ለቦታው ተስማሚዎች የሆኑትን ጉዳዮች እየተመለከቱ መፈ ጸም ለክርስቲያኖች ሁሉ አስፈላጊ ተግባር ነው ፤ ምእመናን ወደቤተ ክርስቲያን መጥተው ሊገበዩት የሚገባ ቸው መንፈሳዊ ተግባር እንጂ ሥጋዊ ተግባርን ስላይደለ በቤተ ክርስቲያን ለጸሎት በሚሄዱበት ወቅት በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚመለከቱትም ሆነ የሚሰሙት ሁሉ መንፈሳዊ ነገርን የያዘ መሆን አለበት ፤ በቤተ ክርስቲያንም አካባቢ ሊሸጡ የሚገባቸው ንዋየተ ቅድሳት ብቻ መሆን ይገባቸዋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ያስተምርበት በነበረው ጊዜ ከዕለታት አንድ ቀን ወደታላቁ ቤተ መቅደስ ሲገባ በዙሪያው የሚሸጡና የሚለወጡ እንስሳዎችንና ዕቃዎችን ተመልክተና ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት የማይፈለጉ ሆነው አገኛቸው በዚህ ጊዜ "ቤቴ ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት ተብሎ ይጠ ራል ፤ እናንተ ግን የሌባ ዋሻ የቀማኞች መሸሻ አደረጋችሁት በማለት የገመድ ጅራፍ አበጅቶ በቤተ መቅ ደሱ ዙሪያና ቅጥረ ግቢ የሚሸጡትን እንስሳ እየገረፈ አስወጥቶ ከማባረሩም ሌላ የለዋጮችን ና የሻጮችን ድርድራቸውን አፍርሶባቸዋል በዚያም አካባቢ እንዳይሸጡና እንዳይለውጡ "ኢትግበሩ ቤተ አቡየ ቤተ ም ስያጥ" የአባቴን ቤት(ቤተ መቅደስ) የመሸጫና የመለወጫ ገበያ አታድርጉ ሲል አስተምሯቸዋል የዮሐ ወን ጌል ፪፡፲፫ ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ከላይ የተጠቀሰውን ውሳኔ ያስተላለፈው ይህንን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ ነው ፤ በዚያ ታላቅ ቤተ መቅደስ ቦታ ተተክታ አሁን የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባት ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያናችን ስትሆን በአንዳንድ ቦታ ላይ የወስላቶች መሸሻ የሸቀጣሸቀጦች መቸርቸሪያ ሁና መቆየቷ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው ፤ ካህናትም ቢሆኑ ይህንን ጉዳይ በቸልታ የተመለከቱት መስለው ቆይተዋል ። ስሕ ተቱ ዓቢይ በመሆኑ በወቅቱ እንዲታረም ትንሣኤ መጽሔትና ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ በትምህርት መልክ መላልሰው ገልጸው ነበር ፤ ነገር ግን አንባቢ እንጂ በሥራ ተርጓሚ ባለመገኘቱ እስከ አሁን ድረስ መፍትሔ ሳይፈለግለት ቆይቷል ።

አሁን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን መርምሮና አጥንቶ አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰዱ ሊመሰገን ይገ ባዋል ። የወሰደውም እርምጃ አስፈላጊ በመሆኑ በእርምጃው የማይተባበሩ ካህናትና ምእመናን ይኖራሉ ብለን አንገምትም ፤ እርምጃው በሥራ ላይ ከዋለ ደግሞ ወደቤተ ክርስቲያን ለጸሎት የሚመጡት ክርስቲያኖች ልቡናቸውን ሳያባክኑ በጽሞና ጸሎታቸውን አድርሰው የሚቻላቸው ሥጋውንና ደሙን ተቀብለው የሚገባው ንም አስተዋጽኦ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥተው በደስታ ወደቤታቸው እንደሚመለሱ የሚያጠራጥር ነገር አይኖ ርም ።

የቅዱስ ሲኖዶስ መልካም እርምጃ በዚሁ ብቻ መወሰን አይኖርበትም ፤ እነዚህን በመሳሰሉ ሕገ ወጦች በሆኑ ድርጊቶች ላይ በየጊዜው የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚደቀኑ ትን ችግሮች እንደሚያስወግድ ተስፋ እናደርጋለን ።

እንደዚሁም በዓመት ፤ በወር በዓላት ፤ በዕለተ እሁድና በዘወትር ቀን በየመንገዱና በየቤተ ክርስቲያኑ ሱቲ ዘርግተው ሥዕል መስቀል ይዘው ደንጊያ ተሸክመው በመለመን ምዕመናንን ግራ የሚያጋቡና በቤተ ክር ስቲያን ቅጽር አካባቢ ሸቀጣ ሸቀጦችን የሚቸረችሩ ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስን ትእዛዝና ውሳኔ በማክበር ወደፊት ከአድራጐታቸው እንደሚታገሡ እናምናለን ፤ አስፈጻሚዎችም ክፍሎች ውሳኔውን ተከታትለው በሥራ ላይ ማዋል አለባቸው ።

## ቤተ ክርስቲያናችን ዳግመኛ ....

ከ፩ኛ ገጽ የዞረ

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ሐዋርያዊ ሥልጣን ባለው ካህን እንደዚሁም በስመ ሥላሴ በውሃ መጠመቁ ከተረጋገጠ ዳግመኛ አታጠምቅም ምክንያቱ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ቢያምኑም ሥልጣነ ክህነታቸው ከሥልጣነ ሐዋርያት የተቋረጠ በመሆኑ ነው ።ሌሎች ደግሞ ሥልጣነ ክህነታቸው በልማድ ሐዋርያ ቢሆንም በትምህርተ ሥላሴ በኩል ጉድለት ይታይበታል ። እንደነዚህ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ካህን የተጠመቀ ጥምቀቱ ተቀባይነትስለሌለው ዳግመኛ ታጠምቀዋለች ።

ነገሩን ግልጽ ለማድረግ አይሁድም ሆኑ ሌሎች አማኞች የመንጻትን ስነ ሥርዓት ይፈጽማሉ ግን ክርስቶሳዊ ጥምቀት አይደለም።በጉባኤ የተወገዙትንስ ጥሮሳውያንና አርዮሳዊያን ያጠመቁት ከዚህ ስለማይሻል ዳግመኛ ይጠመቅ የምትለው ስለዚህ ነው ። በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ ፫ ዳግመኛ ይጠመቁ ሲል ታዞአልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያናችን ዳግመኛ አታጠምቅም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጥምቀት የምታስተምረው ትምህርት በተግባርም የምትፈጽመው ሥነ ሥርዓት ጠለቅ ብሎ ያልገባቸውና ሁኔታውንም ያላጠኑ አንዳንድ ክፍሎች በየዓመቱ የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ የተጠመቁትን ዳግመኛ ታጠምቃለች ። ጥምቀትንም ትከልሳለች እያሉ ጉንጭ አልፋ ወሬ ሲያወሩ ይሰማሉ ከወሬም አልፈው ከመሰሎቻቸውና ለማያውቁትም እውነት በማስመሰል ትምህርት ሲሰጡ ይታያሉ ።

ይህም ከእውነት የራቀ መሆኑን ለማስረዳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ የተጠመቁትን ዳግመኛ እንደማታጠምቅ በጠቅላላው የጥምቀትን ሥነ ሥርዓት እንዴት እንደምትፈጽም በቅደም ተከተል እናሳያለን ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን አባቶች የወሰኑት ውሳኔ በሚያዘው መሠረት የጥምቀትን በዓል በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን እንዲከበር ታደርጋለች ይኸውም በጥምቀት ዋዜማ የከተራ ዕለት ወንዞች ሲፀዱና ሲጠረጉ ይውላሉ ውኃ የሌለበት ቦታ ከሆነ እንደ ወንዝ እየተከተረ ውኃ ተቀድቶ በተከተረው ቦታ ላይ ይሞላበታል ።

ከተራ የሚለው ቃል ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜውም የሚፈሰውን ውኃ መገደብ ወይም ቆርጦ መተው ወይም ጥር ፲ ቀን ለጥምቀት የሚሆን ባሕረ ጥምቀትን ማጠራቀሚያ እንዲሆን ከፈሳሽ ወንዝ የሚከተርበት ቀን ማለት ነው ይህ ሁሉ ተግባር የሚከናወነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተጠመቀበት እንደ ዮርዳኖስ ባህር እንዲሆን ለማድረግ ነው ።

በዚህ አንፃር በኢትዮጵያ ምድር በተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት ያሉት ታቦታት ሁሉ በየአጥቢያቸው በሚገኙት ምዕመናንና ምዕመናት ታጅበው በካህናት ዝማሬ በመንፈሳዊ ወጣቶች መዝሙር በሴቶች ዕልልታ በኅብዛዝት ሆታ እየተዘመረላቸው ወደ ጥምቀተ ባህር ወርደው ያድራሉ ታቦታቱ ባሉበት ድንኳን ዙሪያ ምዕመናን ድንኳናቸውን እየተከሉ በዙሪያው ይከትማሉ ከዚያም አዳር ያደርጋሉ ።

እንዲህ ያለው አደራረግ መነሻ አለ ወይ የሚል ጥያቄ ቢቀርብ መልሱ እንደሚከተለው ይሆናል እያሱ" ሕዝበ እሥራኤልን ወደ ምድረ ርስት ለማስገባት በሚጓዝበት ወቅት የቃል ኪዳኑን ታቦት የያዙትን ካህናትና በጉዞ ላይ ያሉትን የያዕቆብን ልጆች በዮርዳኖስ ባሕር ዳር እንዲያድሩና እንዲከትሙ ነገራቸው እነሱም እግዚአብሔር በኢያሱ አድሮ በነገራቸው መሠረት የዮርዳኖስን ባህር ሳይሻገሩ በዚያው ሰፍረው አደሩ።ማታውንም ኢያሱ ሕዝቡን እንዲህ ነገረው ። "ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ ። ኢያሱም ለካህናቱ የቃልኪዳኑን ታቦት ተሸክማችሁ በሕዝቡ ፊት እለፉ ብሎ ተናገራቸው የቃል ኪዳኑንም ታቦት ተሸክመው በህዝቡ ፊት አለፉ" መጽሐፈ ኢያሱ ም ፫ ከቁጥር ፩-፮ ይህም የሚያሳየን ኢያሱ የጌታቻን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ህዝቡ ያደሩበት ምሽት ደግሞ የከተራ ምሳሌ ይሆናል በማግስቱ የተቀደሱበት ቀን ደግሞ ከውኃና ከመንፈስ ተወልደን የተቀደስንበትና ክርስቶስ በጥምቀቱ መራራ የነበረውን ሐጢአታችን ያጣፈጠበት የጥምቀቱ በዓል ምሳሌ ነው።የቃል ኪዳኑ ታቦትና ካህናቱ ግን ከዚያው ሲያያዝ የመጣ መሆኑን ያሳያል ።

ይህ የመጀመሪያው መረጃ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ያን ግዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙርያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር ። ኢየሱስም በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ" የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፭-፲፮ ።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ከመንበረ ክብሩ ተነስቶ የከተራ ዕለት ወደ ጥምቀተ ባህሩ ወርዶ የሚያድርበት ምክንያት ይህን መሰረት በማድረግ ነው ። ይኸውም ክርስቶስ በዮርዳኖስ የፈጸመውን የጽድቅ ሥራ ለማስፈጸም የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ለመታየት ነው። ከላይ ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ እንደተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዛሬ ጽድቅን እንፈጽም ዘንድ ይገባናል ሲል ከዮሐንስ ጋር ተነጋገረ ። እንዲያጠምቀውም ጠየቀው ።

ይህ ቅዱስ ተግባር በሁለቱ መካከል ከመፈጸሙ በፊት ክርስቶስ ገና አልተጠመቅም ነበር የተነጋገሩበትንም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከተራ ብላ ሰየመች የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ አማኞች ሁሉ በዚህ ቀን ጽድቅን እንዲፈጽምና ታቦቱም ወርዶ በጥምቀተ ባህሩ እንዲያድር ቤተ ክርስቲያን የወሰነችበት ምክንያቱ ይህንን መነሻ በማድረግ ነው።

ሌላው ደግሞ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ውኃ ሲጠመቅ "መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ እርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሰፈረ እግዚአብሔር አብም ይህ ልጄ ነው ቃሉን ስሙት ሲል መሰከረለት" ይህም ለዓለም ሁሉ የተሰጠ መንፈሳዊ ነፃነት ነው ። በመሆኑም ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን በጥምቀተ ባህሩ እየተገኙ የጥምቀትን በዓል ሊያከብሩ ይገባቸዋል ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጠውን የፀጋ ስጦታ ክርስቶስም የፈጸመውን የጽድቅ ሥራ መንፈስ ቅዱስም በየጊዜው የሚያደርገውን የመንፈስ ተሐድሶ የሚቀበሉና ቃሉም በሕይወታቸው የሚሰርጽ መሆኑን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለምታስተምር ነው ።

ለዚህም መረጃ የሚሆነው ወደ ጥምቀተ ባህሩ የሚወርደው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት የተጠማቂው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ታቦቱን ይዘው የሚወርዱት ካህናትደግሞ የአጥማቂው የዮሐንስ ምሳሌዎችና ቸው።ታቦቱን አጅበው የሚወርዱትም



በጥምቀት በዓል ካህናቱ ታቦት ተሸክመው እንደቆሙ ።

ምዕመናንም ክርስቶስ በሚጠመቅበት ጊዜ ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት በዮርዳኖስ ያጠምቃቸው የነበሩት ሕዝቦች ምሳሌዎች ሲሆኑ ጥምቀተ ባህሩ ደግሞ የዮርዳኖስ ምሳሌ ነው ።

በዚህ አኳኋን ካህናቱ የጥምቀት ጥዋት ባህረ ጥምቀቱን ጸልየው ከባረኩ በኋላ በጥምቀተ ባህሩ ዙሪያ የተሰበሰቡትን ክርስቲያኖች ጠበል ይረጩአቸዋል እንጂ አያጠምቁአቸውም ሥነ ሥርዓቱ ያልገባቸው አንዳንድ ክፍሎች ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተጠመቁትን ዳግመኛ ታጠምቃለች ። ጥምቀትንም ትከልሳለች እያሉ ይናገራሉ ። ባይረዱት ነው እንጂ ዳግመኛ አታጠምቅም ። ጥምቀትንም አትከልስም ።

ይህንን አነጋገር እውነት የሚያደርገው እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለ ጥምቀትን በየዓመቱ ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ስናከብር ያዩ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ጥምቀት በኢትዮጵያ ይከለሳል፤ይሰለሳል ብለው ሲጽፉ ሩሲያዊው የጦር መኮንን ቡላቶቢች ከእንጦጦ እስከ ባር ወንዝ ድረስ" በሚለው መጽሐፈ ጥምቀት በኢትዮጵያ የማይመለስ የማይከለስ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ሲገልጥ እንዲህ ይላል።" ጥቂቶች የውጭ ሀገር

ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ እንደሚጠመቁ ይናገራሉ ፣ ይኸውም በዓለ ጥምቀት በሚከበርበት ቀን ነው። ሆኖም ይህ አነጋገራቸው ፍጹም ስሕተት የተመላበት ነው በሃይማኖት ጸሎታቸውና በምዕላዳቸው የተደነገገው ጥምቀተ ክርስትና የሚፈጸመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ሆኖም ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ይጠመቃሉ ክርስትና ይነሣሉ የሚለው ሥህተት የመጣው ኢየሱሳውያን በተቀደሰው በዮርዳኖስ ውኃ ምሳሌ የተባረከውን ውኃ ኢትዮጵያውያን ቀሳውስት ሕዝቡን ሲረጩ ሕዝቡም በባሕረ ጥምቀቱ ሲዋኙ ስላዩ ነው ለምሳሌ እኛ ሩሳውያን አንድ ልምድ አለን በዮርዳኖስ ውኃ ምሳሌ የተቀደሰውን ውኃ እንረጫለን የቻለም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በዮርዳኖስ ውኃ ይጠመቃል ። (ይዋኛል)እኔ ራሴ ምስክር ነኝ ኢትዮጵያ በነበርኩበት ጊዜ በዓለ ጥምቀትን አብሬ አክብሬአለሁ ። ኢትዮጵያዊው ቄስ ሦስት ጊዜ ውኃውን በራሴላይ አፈሰሰብኝ ሥርዓተ ጥምቀት ተፈጸመለት ወይም ክርስትና ተነሳ ብሎ ያሰበ ማንም ኢትዮጵያዊ አልነበረም" በማለት ጥምቀት በኢትዮጵያ የማይመለስ የማይከለስ መሆኑን ለሩሲያ ሕዝብ አስረድቷል ።

ይህ የተገኘው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ከሩሲያ አብዮት በፊት ከሚለው ጽሑፍ ነው ።

ይህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ዳግመኛ አታጠምቅም ማለት ነው ለምሳሌ በሕፃንነቱ ከተጠመቀ ካደገ በኋላም እምነቱን ቢክድ ፣ ክርስቲያናዊ ሕይወቱንም ባያስተካክል ስለ መጀመሪያ ጥምቀቱ ትምህርት ሰጥታ በንስሐ ትቀበለዋለች እንጂ ዳግመኛ አታጠምቀውም ይሁን እንጂ በሌላ ቤተ ክርስቲያን የተጠመቀ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቢመለስ ቀድሞ ስለ ተቀበለው ጥምቀት ልዩ ጥንቃቄ ታደርጋለች ። ይህም ማለት አንደኛ የአጥማቂውን ሥልጣነ ክህነት የተጠመቀባቸውን የመንፈስ መሳሪያዎች ትመረምራለች ። ሁለተኛ አጥማቂው ከሐዋርያት ሲያያዝ የመጣው ሥልጣነ ክህነት ያልተቋረጠበት መሆኑን ታጣራለች ። ሦስተኛ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ የተጠመቀ መሆኑንና አለመሆኑን ለመረዳት ትፈልጋለች ።

ወደ ፫ኛ ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

## "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ"

"እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" በማለት ስለራሱ የተናገረው ቃል ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢርን የያዘ ነው ። ብርሃን የሕይወት ሁሉ ምንጭ እንደሆን ክርስቶስ የሕይወት ባለቤት ነው ። ሕይወትን ይሰጣል ፣ መስጠት ብቻ ሳይሆን ሕይወትን ይፈጥራል ” እውነተኛ ብርሃን ከእውነተኛ ብርሃን፣እውነተኛአምላክ ከእውነተኛ አምላክ ነውና ” ያለ ብርሃን ብርሃንን ማየት እንደማይቻል ሁሉ ያለ እውነተኛው ብርሃን እግዚአብሔርን ማየት የቻለ ማንም አልነበረም ። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመጣ በኋላ ግን ወልድን ያየ አብን እንዳየ ተቈጠረለት አብና ወልድ አንድ ናቸውና ። ስለዚሁም ቀሌምንጦስ ዘሮሜ . እንዲህ ይላል በብርሃን ክርስቶስ እግዚአብሔርን እናያለን ፣ በክርስቶስ ዓይነ ልቡናችን ሁሉን ለማየት ይገለጣል ። በክርስቶስ አእምሮአችንና መንፈሳዊ ስሜታችን ይከፍታሉ ”

አዎ በክርስቶስ ሁሉ ነገር ተገልጦአል ። በክርስቶስ መምጣት እግዚአብሔርንና ሰውን ለያይቶ የነበረው የኃጢአት መጋረጃ ስለተቀደደ ሰዎች እግዚአብሔርን አዩ ። እግዚአብሔርም ወደ ሰዎች ተመለከተ ።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃንነት በብዙ መንገድ ነው ። ለምሳሌ በተወለደበት ሌሊት በቤተልሔም አካባቢ ለነበሩ እረኞች የእግዚአብሔር ክብር እንደ ታላቅ ብርሃን አበራላቸው በብርሃኑም ተመርተው ወደ እውነተኛው ብርሃን ክርስቶስ ደርሰዋል (ሉቃ ፪፡፱)። ሰብአ ሰገልም በኮከብ ብርሃን እየተመሩ ሄደው "እኔ የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነኝ" (ራእ.፳፪፡፲፮) በማለት የተናገረውን ክርስቶስን አግኝተዋል ። ከዚያም በኋላ ራሱ መድኃኒታችን ክርስቶስ በገሊላ የማስተማር ሥራውን ሲጀምር 'በጨለማ ለሚኖሩ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ወጣላቸው ” በማለት መለኮታዊ ትምህርቱ ሕይወት ሰጭ ብርሃን መሆኑን ገልጦአል ።

ከዚህም ጋር ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ ለተወለደው ሰው ዐይን በመፍጠሩ በልዩ ልዩ ምክንያት የታወሩም እንዲያዩ በማድረጉ እውነተኛ ብርሃንነቱ ታውቋል ።

የትምህርተ ሃይማኖት ሊቃውንት ለፀሐይ ሦስትነት (ክበብ ብርሃን ፣ ሙቀት) እንዳለው ይናገራሉ ። በዚህም የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት መስለው ያስተምራሉ ። በዚህ ትምህርት መሠረት በብርሃን የሚመሰለው ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ነው ።

ምክንያቱም ብርሃን ከክበቡ ሳይለይ ወደዚህ ዓለም ደርሶ ከፍጡራን ዐይን ጋር እንደሚዋሐድ እግዚአብሔር ወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ባለመለየት ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ተዋሕዶአልና።ብርሃን ከዐይን ጋር ሲዋሐድ ዐይንን አይለውጥም ። ወልድም በማሕፀነ ድንግል ማርያም በተፀነሰ ጊዜ ማሕተመ ድንግልናዋን አልለወጠም ።

የብርሃን ምንጭ የሆነው ፀሐይ ከዚህ ዓለም (ምድር) በብዙ ሚልዮን የርቀት መለኪያ የሚቆጠር ርቀት ሲኖረው ርቀቱ ሳይወስነው ብርሃኑ በዚህ ዓለም እጅግ ጎልቶና ደምቆ ያበራል ። እግዚአብሔር ወልድ ክርስቶስም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጽርሐ አርያም በዘባነ ኪሩቤል ተቀምጦ ቦታ ሳይወስነው ይህን ዓለም ይመግባል ። ጥልቁንና ከጥልቁ በታች ያለውን ሁሉ ይመለከታል ያውቃልም ።

ይህንም በማስተዋል ኢትዮጵያዊው ሊቅ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደረሰው መልክዐ ጨለማን ያስወገድህ ብርሃን ክርስቶስ ሆይ በኪሩቤል ላይ ተቀምጠህ ጥልቆችን ታያለህ ” ብሏል ።

እንግዲህ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" በማለት ስለራሱ የተናገረው ቃል ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን መንፈሳዊ ትርጉም ሁሉ የሚያስረዳ መሆኑ ግልጥ ነው ።

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ከልደት በፊት ካሉት ስድስት ሳምንታት መካከል አንዱ ሳምንት "ብርሃን" እየተባለ ይጠራል ። ይህም በጨለማ ውስጥ ያሉ ሰዎች ጨለማው ወይም ሌሊቱ አልፎ የቀኑን ብርሃን ለማየት እንደሚናፍቁ በኃጢአት ጨለማ ውስጥ የነበሩ ሁሉ ትንቢቱ ሲፈጸም የእግዚአብሔር ወልድን ወደዚህ ዓለም መምጣት መጥቶም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድናቸው በተስፋ መጠባበቃቸውን ያመለክታል ።

በዚህ ሳምንት ስለ ክርስቶስ እውነተኛ ብርሃንነት የሚገልጡ ክፍሎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ይነበባሉ ይተረጐማሉ ብርሃንህንና እውነትህን ላክልን ” የሚሉት መዝሙራት ይዘመራሉ ። በዚህ ሳምንት ምእመናን ሁሉ ለብርሃን ልደቱ ያድርሰን ያድርሳችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን እርስ በርሳቸው ይገልጣሉ ።

እነሆ እውነተኛ የዓለም ብርሃን እንደሆነ የተናገረው ክርስቶስ ዛሬም በራስ ወዳድነት ባልንጀራን በመጥላት ፈጣሪውንም በመዘንጋት ዕውር በሆነው በዚህ ዓለም "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ እኔን የሚከተለኝ በጨለማ አይመላለስም" እያለ በሕያው ቃሉ ይናገራል ይህን ቃሉን ሰምቶ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት ይሸጋገራል በዚህ በጨለማው ዓለም አይደናገርም ። ሕይወት ምን እንደሆነ ያስተውላል። ከጨለማው ዓለም ባሻገር ምን እንዳለ ያውቃል ።

ታዲያ ብርሃን ክርስቶስን ለመከተል ጊዜው ዛሬ ነው ። ስለዚህ "አንተ የተኛህ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል ” (ኤፌ.፭.፲፬) የተባለውን ቃል ማስተዋል ለሁሉ ይጠቅማል ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ሴቶች በማህበራዊ ኑሮ

ማኅበራዊ ኑሮ የተመሠረተው በአንዲት ሴትና በአንድ ወንድ መካከል ነው ። መቼም ሆነ የትም የአንድ ሕብረተሰብ ምንጭ ቤተሰብ መሆኑ እሙን ነው በመሆኑም ወንድ ብቻውን ማህበራዊ ኑሮን ለመመሥረት አይችልም ።

ማኅበራዊ ኑሮ የሚመሠረተው አብሮ በመኖር ሲሆን መኖርም እንደሚታወቀው ከሰው ልጆች ጋር እንጂ ከእንስሳት ጋር አይደለም የሰው ዘርም ሊበዛ የሚችለው በሴቶች አማካኝነት ስለሆነ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት የተመሠረተው ኑሮ ወደ ቤተሰብነት ያመራና ከጠባቧ ቤተሰብ የሚውጣጣውም ሕብረተሰብ ሰፊውን ዜጋ ሊገነባ ይችላል። በዚህ አንጻር ሴቶች ለማህበራዊ ኑሮ መሠረት፣ማዕከልና መዋቅር ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም ።

ቤተሰብን ለማደራጀትና ለማበርከት ከሴቶች የቀረበ ኃላፊ የለም ። ከጥሩ ቤተሰብ የተውጣጣው ሕብረተሰብም ጥሩ ዜጋ መሆኑ አያጠራጥርም ። ጥሩ እናት ለማህበራዊ ኑሮ ጥሩ ልጅ ታበረክታለች ። ብዙውን ጊዜ የቤተሰብ ሃላፊዎች እናቶች ፣ ስለሆኑ ልጆችም በይበልጥ የእናቶቻቸውን ፈለግ ይከተላሉ ። በቤት ውስጥ የሚገኘውን የሥራ ድርሻ ለቤተሰቡ የሚደለድሉ እናቶች በመሆናቸው ልጆችም የእናቶቻቸውን ትእዛዝ በማክበር የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ያከናውናሉ ።

እንዲያውም ሴቶች በቀድሞው የጋርዮሽ ስርዓተ ማህበር ተብሎ ይጠራ በነበረበት ዘመን የሥራ ድልድል ስለነበር ወንዶች ለአደን ሲሄዱ ሴቶች ልጆችን ማሳደግ ፍራፍሬ መልቀም በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙትን ትናንሽ አውሬዎች ማደን የነርሱ ሥራ ነበር ። ይህ ሊሆን የቻለው ወንዱ ከአደን የሚያመጣው የማያስተማምን ስለነበረ ብዙውን ጊዜ ኅብረተሰቡ ለምግብ የሚመካው ሴቷ ለቅማ በምታመጣው ፍራፍሬ ስለነበረ ነው ። በዚያ ዘመን የሚወለዱትም ልጆች ዝርያቸው የሚቆጠረው በእናታቸው በኩል ብቻ ነበር ። ዘመኑም "የእናት ዘመን" በመባል ይታወቅ ነበር ።

እንደዚህም ሁሉ የዚህን ተመሳሳይ የሆነ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ አንዳንድ ቦታ ተጠቅሶ እናገኛለን ።

" ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ቀን ነው መከራም ይሞላዋል" ይላል መጽሐፈ ኢዮብ ም.፲፬.ቁ ፩ " እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል" ማቴ. ም. ፲፩ ቁ ፲፩ ፣

ይህ እንግዲህ የሚያመለክተው በዚያ ወቅት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ከፍ ያለ ታዋቂነትና የበላይነትም እንደነበራቸው ነው ።

በአሁኑ ጊዜም በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙት የሃገራችን ሴቶች በማህበር በመጠናከርና ያልተማረውንምኅብረተሰብ በማስተማር ልዩ ልዩ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን በመርዳት በጠቅላላው ያላቸውን እውቀትና ንብረት ከጥቅም ላይ በማዋል እንደሚገኙ ከታሪክ ማህደር ለመረዳት ይቻላል ለቤተሰብና ለኅብረተሰቡ በማህበራዊ ኑሮ ረገድ የተቸገሩትን ሁሉ በመርዳት ረገድ ያደረጉትና የሚያደርጉት ጥረት በጣም ከፍ ያለ ነው ።

አንድ አገር በኢኮኖሚ በማህበራዊ ኑሮ በባህልና ሌላም እነዚህን በመሳሰሉት መሻሻልና መደራጀት የሚቻለው ፆታና ዕድሜ ሳይለዩ በጠቅላላው በኅብረት ሲበለጽግ ነው ። ሴቶችም ለእናት ሃገራቸው የሚያደርጉት የሥራ አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም በጦር ሜዳ በመሠማራት የሚፈለግባቸውን ግዴታ ከወንዶች ጐን ተሰልፈው ልዩ ልዩ ጀብዱዎችን ፈጽመዋል በመፈጸምም ላይ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ሴቶች በልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ተግባሮች መሠማራት የሃገሪቱን የእጅ ጥበብ ሥራ ለማሻሻልና ከፍ ለማድረግ ይረዳል ተብሎ ተገምቷል።በሕክምናም ሆነ በልማት ሥራው ሁሉ እንደዚሁ ያላደረጉት የሥራ እርምጃ የለም በቤተ ክርስቲያንም ሥራ እንደዚሁ በሚመለከታቸው የሥራ ቦታዎች ሁሉ ተሰማርተው አገልሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።

ሴቶች ያወቁትን ለማሳወቅ የተማሩትን ለማስተማር ሃላፊነቱ የመንግሥት ብቻ ያለመሆኑን በማወቅ በአሁኑ ወቅት የሚያደርጉት ጥረት በቂ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል ።

ከዛሬ ጀምሮ በዚህ አምድ ስለ አንዳንድ የምግብ ዓይነቶች አሠራር በአጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን እናንተም የምታውቁትን ያህል ጽፋችሁ ብትልኩ

ተከታዩ ወደ ገፅ ፲፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ልማት በቤተ ክርስቲያን ስንል ለመግለጽ የምንፈልገው በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር የሚኖሩትን ካህናት የልማት እንቅስቃሴ ነው ።

ስለዚህ በከተማም ሆነ በገጠር ፣ በገዳማትም ሆነ በአድባራት የሚገኙ ካህናት ሁሉ የሚያደርጉትን የልማት እንቅስቃሴ ራሳችን ወደቦታው ሄደን በመመልከትና በዳብዳቤም የሚገልጹልንን በመጽሔታችን እያሳተምን በማውጣት ለአንባብያን እናቀርባለን ።

በዛሬው እትማችን የምንገልጸው በወሎ ሀ/ ስብከት በደሴ ከተማ የገነተ ጊዮርጊስ ደብር ካህናት የሠሩትንና የሚሠሩትን የልማት ተግባር ነው የደሴ ገነተ ጊዮርጊስ ደብር ካህናት ከሰበካ ጉባኤው አባላት ጋር በመተባበርና በመመካከር ከ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. ጀምረው እስከ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ድረስ "እያመረትን እንቀድሳለን እየቀደስን እናመርታለን" በማለት በደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ተስፋ ወ/ አብርሃም አስተባባሪነት በርከት ያሉ የልማት ተግባሮችን አከናውነዋል ፣ አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛሉ ከሠሩአቸውም የልማት ተግባሮች በደብዳቤ ተመዝግበው የደረሱን የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. ካህናቱ የከፍተኛ አንድ ቀበሌ 7 ከነማ ጽ/ቤት በአደረገላቸው መልካም ትብብርና በተሰጣቸው የልማት ቦታ ላይ በዶማ ቆፍረው በቆሎ ፣ ካሮት በርበሬ ጥቅል ጎመን ወዘተ ... የመሳሰሉትን ተክለው በተገኘው ውጤት ችግራቸውን አስወግዋል ፣ ይኸውም በገንዘብ ሲተመን ብር ፫፻ ይሆናል ።

2ኛ/ በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. በዚህ ለልማት በተፈቀደው ቦታ ላይ ገብስ ዘርተው ሃያ አንድ ኩንታል አምርተው ከዚሁ ፳፩ ኩንታል ገብስ ላይ ፭ ኩንታል ለቤተ ክርስቲያኑ ገቢ አድርገው የቀረውን ፲፮ ኩንታል ገብስ ለችግራቸው ማስወገጃ ይሆናቸው ዘንድ ተከፋፍለውታል፣ ይኸውም በገንዘብ ሲተመን ብር ፬፻፶፭ የሚያወጣ መሆኑ ታውቋል ።

፫ኛ/ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ተራድኦ መምሪያ አንድ ጥንድ በሬ ገዝቶ ስለሰጣቸው ተጨማሪ የልማት ቦታ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ካህናቱ የከፍተኛ ፩ ቀበሌ ፯ ከነማ ጽ/ቤትን የልማት ቦታ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ፭ ሄክታር መሬት ስለሰጣቸው በድምሩ ፲፭ ሄክታር መሬት ለልማት የሚሆን አግኝተዋል ። በዚሁም ቦታ ላይ ጤፍ ዘርተው አሁን ጤፉን በመንከባከብ ላይ ይገኛሉ ፣ የጤፉም አዝመራ እንደሚገመተው ተወቅቶ ሲገባ ከ40 ኩንታል በላይ እንደሚሆን ሲገመት ይህ በመካከለኛ ደረጃ በገንዘብ ሲተመን በአንድ ኩንታል ብር ፸፭ ሂሳብ ሶስት ሺህ ብር እንደሚያወጣ ተገምቷል ።



መልአከ ገነት ተስፋ ወ/አብርሃም የደሴ ገነት ጊዮርጊስ ደብር አስተዳዳሪ

፬ኛ/ ለደሴ ገነተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በተፈቀደው የልማት ቦታ አካባቢ ካህናቱ ስድስት ሺህ የችግኝ መትከያ ጉድጓድ ቆፍረው የባህር ዛፍ ተክለው ሁሉም ስለ በቀለ አሁን አጥሩን በማጠርና ችግኙንም በመኮትኮትና በመንከባከብ ላይ ይገኛሉ ።

፭ኛ/ በገንዘብም አስተዋጽኦ በኩል ካህናቱ ብዙ አስተዋጽኦን አድርገዋል ለምሳሌ የደሴ ገነተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለበት ቦታ ላይ የተመሠረተው በ፲፱፻፬ ዓ.ም. ሲሆን ከጊዜ ርዝመት የተነሣ የቤተ ክርስቲያኑ ግንብ በመሰንጠቁ ለግንቡ ማሰጠገኛ እንዲሆን ከምእመናኑ የተሰበሰበው ገንዘብ በቂ አለመሆኑን ካህናቱ ተረድተው ለቅዱስ ዮሐንስ በዓል (ለዘመን መለወጫ) በድጉማ መልክ የሚሰጣቸውን አንድ ሽህ ብር ለቤተ ክርስቲያኑ ማስጠገኛ እንዲሆን በገዛ ፈቃዳቸው ለግሠዋል ፣ በተጨማሪም ስለዚሁ የልማት ይዞታ እንዲያብራሩልን የደብሩን አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ተስፋ ወ/ አብርሃምን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ።

ጥያቄ "እየቀደስን እናመርታለን እያመረትን እንቀድሳለን" በሚል ዓላማ በመነሣት በልማቱ ተግባር የተሠማሩት ካህናት ስንት ናቸው ?

መልስ ፦ በልማቱ ሥራ ተሰልፈው የሚሠሩት ካህናት ፵ ሲሆኑ እነርሱም ቀሳውስት ፣ ዲያቆናትና መዘምራን ናቸው የሰበካ ጉባኤ አባላትም በዚህ የልማት ተግባር ከካህናቱ ጋር በመተባበር ካህናቱን በአሳብም ፣ በሥራም በገንዘብም ይረዳሉ ።

ጥያቄ ፦ አንዳንድ ካህናት በመጀመሪያ የልማቱን ተግባር በጋለ መንፈስ ተነሣሥተው ይጀምሩና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሥራውን ያቀዝቅዙታል ፈጽመው ከመተውም ደረጃ የደረሱ አሉ ስለዚህ ሥራው እንዳይቀዘቅዝ ምን የወሰዳችሁት እርምጃ አለ ?

መልስ ፦ በልማት ተግባር ለተሠማሩት ካህናት በዓመት አንድ ጊዜ በድጉማ መልክ አንዳንድ ስጦታዎችን እናደርጋለን የሚደረገው ስጦታ ለካህናቱ የሞራል ድጋፍ ስለሚሆናቸው የልማቱን ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደጉት ይሄዳሉ እንጂ ከመሥራት ወደኋላ አይሉም ።

ጥያቄ ፦ በደሴ ከተማና በዙሪያው ያሉት አብያተ ክርስቲያናት እንደ እናንተ ያለ የልማት ተግባር እንዲሠሩና ራሳቸውንና ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት እንዲችሉ ምን ዓይነት ምክር ሰጥታችኋቸዋል ?

መልስ ፦ እርግጥ ነው በደሴ ከተማ ፯ አድባራት አሉ እነርሱም በኅብረት ሆነው የልማት ተግባር ጀምረው እንዲሠሩ ሀ/ስብከቱ መመሪያ አውጥቶ ሰጥቶአቸው ጀምረው ነበር ፣ ነገር ግን አንዱ ከሌላው ጋር ባለመስማማት የልማቱ ሥራ ሊቋረጥ ችሏል ያ ስለተቋረጠ እኛም ለግላችን ተለይተን ይህንን የልማት ተግባር ጀምረናል።እኛ በሚገባ ሥራችንን ከአጠናከርን በኋላ የቀሩትን አድባራት በመቀስቀስ የልማት ሥራ እንዲሠሩ ለማድረግ ምኞት አለን ። ይህ እኛ የምናደርገው የልማት እንቅስቃሴ በመጽሔት ታትሞ ሲወጣ ለቅስቀሳው ተግባር አመቺ እንደሚሆንልን እንተማመናለን ።

ጥያቄ ፦ እናንተ እየቀደስን እናመርታለን እያመረትን እንቀድሳለን በማለት ተነሣታችሁ የልማቱን ተግባር በሚገባ ማከናወናችሁ እሙን ነው ። ይህም እጅግ የሚያስደስት ተግባር በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ታመሰግናችኋለች ወደፊትም በዚህ ብቻ ሳትወሰኑ እንድትጨምሩበት በርቱ የሚለውን ቃል ቅ.ቤተ ክርስቲያናችን ታበሥራችኋለች ፣ ነገር ግን የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያናችን የልማት መሠረት ትምህርት ነው ትምህርት ከሌለ መቀደስ ማኅሌት መቆምም ማስተማርም አይቻልም ስለዚህ በትምህርት በኩል ያላችሁን ይዞታ ቢገልጹልን ?

መልስ ፦ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አጠናቀው የተማሩ መምህራን ስላሉን አሁንም እነርሱ በማስተማር ላይ ይገኛሉ ። ወደፊትም ተጨማሪዎች መምህራንን ቀጥረን እንዲያስተምሩ ለማድረግ አስበናል ።

ጥያቄ፦ወደፊት ስለልማቱ ያላችሁ ዕቅድ ምን እንደሆነ ቢገልጹልን ?

መልስ ፦ በልማቱ ተግባር በምናገኘው ገንዘብ በአካባቢያችን ያሉትን ረዳት አጥተው የሚቸግሩትን ድኩማን አጥተው የሚቸግሩትን ድኩማን የምንረዳበትንና የምንከባከብበትን ዘዴ መኪና ገዝተን ልብስበመስፋት፫ኛ ላምና ዶሮ ገዝተን በማርባት የገቢያችንን ምንጭ በርከት አድርገን የካህናቱን ኑሮ ለማሻሻል ሰፋ ያለ ዕቅድ አለን ።



ካህናቱ በልማት ሥራ ላይ

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ከአሁን ቀደም አንድ ጥንድ በሬ ገዝቶ በመስጠት እንደረዳን ወደፊትም የስፌት መኪና ፣ የላምና ዶሮ መግዣ እንዲሰጠን ጠይቀናል ጥያቄያችን ግቡን የመታ እንደሆነ የልማቱም ተግባር በበለጠ ያማረና የሠመረ ይሆናል ሲሉ መልአከ ገነት ተስፋ አሳባቸውን ደምድመዋል ። የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት የሚያከናውኑአቸው የልማት ሥራዎች ለቤተ ክርስቲያናችን የተሐድሶ መንገድ ጠራጊዎች ለመሆን ስለሚችሉ ካህናት የሆኑ ሁሉ እጆቻቸውን ወደልማትና ተግባረ ዕድ የመዘርጋት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ቀን ሕዝቡን ሲያስተምርና ሲመክር እየዋለ ሌሊት በሚሠራው ተግባረ ዕድ ውጤት ይመገብ ነበር እንጂ ቀን የሚያስተምራቸው ሕዝቦች ይቀልቡኝ የሚል አስተሳሰብ አልነበረውም ይህንንም ሲገልጽ "ከማንም ብር ፣ ወርቅ ፣ ልብስ አልተመኘሁም እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልጉኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉ እንዲያገለግሉ እናንተ ታውቃላችሁ እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታችን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ" ብሏል የሐ. ሥራ ምዕ.፳ ቁ ፴፬ - ፴፭ ።

ሐዋርያው ሠርቶ ያሳየው በጊዜው ለነበሩት ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሡ ካህናትም ስለሆነ ሁሉም ካህናት ለልማት ተግባር ተሠልፈው የመሥራት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል ።





www.ethiopianorthodox.org

# የእግዚአብሔር መገለጥ

እግዚአብሔር አይታይም ። ደግሞም አይመረመርም ። ስለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም ። በማለት ተናግረዋል ። ይሁን እንጂ አለመታየቱ ወይም አለመመርመሩ ህልውናውን አያስተባብልም ።

ጠቢባን ሰዎች በጥበብ መንገድ እግዚአብሔርን መመርመርና ማግኘት አይችሉም ። በሰው ሠራሽ መሣሪያ ተመርምሮ የሚደርስበት ፍጡር የሆነ ነገር ብቻ ነው ። እግዚአብሔር ግን ፈጣሪ ስለሆነ የሰዎች ፍልስፍና አይደርስበትም ።

እግዚአብሔር እንደዚህ የማይታይ ከሆነ ሰው ስለ እግዚአብሔር ህልውና እንዴት ለማወቅ ቻለ ? ለዚህ ጥያቄ ቀላሉ መልስ ሰው የእግዚአብሔርን ህልውና ለማወቅ የቻለው ራሱ እግዚአብሔር በፈቃዱ ራሱን ስለገለጠ ነው የሚል ይሆናል ። ፀሐይን ያለ ፀሐይ ማየት እንደማይቻል ሁሉ ሰው ያለ እግዚአብሔር ረድኤት ስለ እግዚአብሔር መማርና ማወቅ አይችልም ። እእምሮውና ችሎታው የተወሰኑ ናቸውና ። ሰው ኃጢአተኛ ስለ ሆነ ንጹሕና ቅዱስ የሆነውን አምላክ ለማየት ኃጢአቱ ይከለክለዋል ።

ግን እግዚአብሔር ውሱንና ኃጢአተኛ ለሆነው ሰው ራሱን ገልጦአል ። የእግዚአብሔር ህልውና በታሪክና በሥነ ፍጥረት ፍጹም ሥነ ሥርዐት ታውቆአል ።

የእነዚህም አስረጅነት እንደሚከተለው ነው ። ማንኛውም ነገር ያለ ምክንያት አይገኝም አንቀሳቃሽም የሌለው ተንቀሳቃሽ የለም ። ይህም እውነት አስደናቂ የሆነውን ሥነ ፍጥረት የተሞላው ዓለም በራሱ አልተፈጠረም ወደሚለው ሀሳብ ያደርሳል ። ይህ አስደናቂ ዓለም እጅግ ዐዋቂ በሆነው ፈጣሪ በእግዚአብሔር ተፈጥሮአል ሥነ ፍጥረት በጥልቅ የሚመለከተውን ሁሉ ወደ ፈጣሪው ይመራል ይህን የተረዱ ቅዱሳን ሰዎች እንዲህ ብለዋል “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ። የእጁንም ሥራ ይመሰክራሉ” (መዝ.፲፰ ፣፩)

የማይታይ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ይታወቃል (ሮሜ. ፩፡ ፳) በኋላ የተነሡ ሊቃውንትም በዙሪያችን ያሉ የሚታዩ ነገሮች ሁሉ ስለማይታየው እግዚአብሔር ያስተምሩናል ብለዋል ።

ከዚህ ጋር የእግዚአብሔርን መኖር (ህልውና) የሚገልጥ የሥነ ፍጥረት ፍጹምነት ወይም ሥነ ሥርዐት ነው ። “ማንኛውንም ነገር በጥበብ አደረግህ” ተብሎ በነቢዩ ዳዊት እንደተነገረ ለዘለዓለም የማይናወጠውና የማይዛባው የተፈጥሮ ሥነ ሥርዐት አንድ ፍጹም ዐዋቂ የሆነ ፈጣሪ መኖሩን ያስረዳል ። ይህ በሕግና በሥነ ሥርዐት የሚራመደው ዓለም ራሱ በራሱ ተገኘ ተብሎ ሊገመት አይቻልምና ።

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ሌላው መንገድ ደግሞ ታሪክ ነው ። በዘመናት መካከል በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ያለው የሰዎች ታሪክ በምድር ላይ አምላክ የሌለው ሕዝብ እንዳልኖረ ያስረዳል ።

በዓለም ውስጥ የሰው ልጆች ሁሉ ታሪክ ሲመረመር በአምልኮት ማመን በጣም የተለመደ ሕግ ሆና ተገኝቶአል። የሰው ዘር ከራሱ የሚበልጠውን ኃይል ለማምለክ ያልሞከረበት ጊዜ ፈጽሞ አልነበረም ።

እንግዲህ አምላክ ባይኖር ሰውን ወደአምልኮት የሚስብጠባይከየትመጣ?ከመሬትወርቅናአልማዝባይኖሩኖሮ የሰው ልጆች መሬትን ለመቆፈር ባልደከሙም ነበር ። በዚህ አንጻር የሰውን መንፈስ ወደ እርሱ የሚማርክ እውነተኛ አምላክ መኖሩን ማመን ግድ ነው።

እስካሁን የእግዚአብሔር ህልውና የተገለጠባቸው መንገዶች ሁሉ አጠቃላይ ከመሆናቸውም በላይ የእግዚአብሔርን አካላዊነት አያስረዱም ። ስለሆነም እግዚአብሔር ራሱን በሌላ መንገድ ገለጠ ። የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ። ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ። እነሆ በዚህ ጊዜ የማይታየው ታየ ። ረቂቅ በግዙፍ ተገለጠ ፤ የማይዳሰሰው ተዳሰሰ ። የሰው ልጆች ሁሉ በሥነ ፍጥረት የተመለከቱት በሞራላዊ ሕግ የተረዱት በታሪክ ያስተዋሉት ። በሥነ ፍጥረት ፍጹም ሥነ ሥርዓታዊ ጉዞ ያደነቁት አምላክ በሥጋ ተወልዶ በገሀድ በመካከላቸው ተመላለሰ ። ከሰው ልጆች ጋር አብሮ በላ ፤ ጠጣ ። በፈቃዱ ሰው እንደመሆኑ የሰውን ሕግ ፈጸመ ።

እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠበት አምላክነቱም ለሰዎች በግልጥ በዩርዳኖስ የተመሰከረበት ክፍለ ጊዜ “አስተርእዮ” ወይም “ዘመነ አስተርእዮ” እየተባለ በየዓመቱ በታላቅ ሃይማኖታዊ ሥርዐት ይታሰባል ። አንዳንድ ጊዜም አስተርእዮ ማርያም ይባላል ። ይህም እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ መገለጡን ያሳያል በሌላም (ግሪክ) ቋንቋ ኤጲፋንያ ተብሎ ይጠራል ። ሁሉም የሚያመለክተው የማይታየው ረቂቅ አምላክ በሥጋ መገለጡን ነው ።

በዚህ እውነተኛ የእግዚአብሔር መገለጥ ላይ የክርስትና እምነት ተመሥርቶአል ። ክርስቲያኖች የሚያመልኩት አምላክ በሥነ ፍጥረትና በታሪክ የታወቀ በመጨረሻም በሥጋ የተገለጠ አምላክ ነው ። ክርስቲያን የማይታወቅ አምላክን አያመልክም ። ክርስቲያን በሆነ ባልሆነው አይሸበርም ። ጽጥ ያለና የረጋ መንፈስ አለው ፤ ምክንያቱም ፈጣሪውን ያወቀ ፈጣሪውም ከእርሱ ያልራቀ ነውና ፤ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንዴት መቸ አያለሁ? ብሎ አይጠራጠርም ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እኔን ያየ አብን አየ ባለው መሠረት እግዚአብሔርን አይቶአልና ።



## ሴቶች በማህበራዊ....

ከ፮ ገጽ የዞረ

ልን ለዚህ አምዳችን ያላችሁን ተባባሪነት ይገላፃል እንግዲህ ለዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ስለ ሙዝ ኬክ አሠራር ይሆናል ።

መንፋት ነው ከዚህ በኋላ እንቁላሉንና ከዚያም በርከት ያለ ዘይት ጨምሮ

### የሙዝ ኬክ

የሙዝ ኬክን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ነገሮች

፩. የፉርኖ ዱቄት አንድ ብርጭቆ ተኩል

፪. ትንሽ ጨው

፫. አንድ ትልቅ እንቁላል

፬. ወተት ከግማሽ ብርጭቆ በላይ

አሠራሩ እንደሚከተለው ነው

ዱቄትና ጨውን ባንድ ላይ በወንፊት መንፋት ነው ከዚህ በኋላ እንቁላሉንና ትንሽ ወተት ጨምሮ በቀስታ በጎድጓዳ ሣህን ውስጥ መምታት ያስፈልጋል ። የቀረውን ወተት ትንሽ በትንሽ ጨምረው ሁሉንም አንድ ላይ ተቀላቅሎ ይመታ ወፍራም መሆን አለበት የሚቀጥን ከሆነ ወተቱን በሙሉ መጨመር አስፈላጊ አይደለም ። በቂ ወተት ከተጨመረ በኋላ ደህና አድርጎ መትቶ ለሠላሳ ደቂቃዎች ያህል እንዳለ መተው ነው ከዚያም በርከት ያለ ዘይት ጨምሮ መጥበሻውን በጣም ማሞቅ ያስፈልጋል ።

አሁን ሙዞችን አራት ቦታ ላይ ወደ ታች በመሠንጠቅ ተበጥብጦ ከተቀመጠው የፉርኖ ዱቄትና እንቁላል ውስጥ ነክሮ በፈላው ዘይት ጠብሶ ወዲያውቀላ ሲል ማውጣትና ትንሽ ስኳር ነስንሶ መብላት ነው ። የተጠበሰው ሙዝ ከመጥበሻው ሲወጣ መልኩ ልክ የአሣ ጥብስ ይመስላል ጣእሙማ ይተውኝ አንድ ቀን ይሥሩና ይቅመሱት ከዚያ በኋላ ማዘወትርእንግዶችዎን ሊጋብዙዋቸው የሚፈቅዱት ግሩም ምግብ ይኸ ብቻ እንደሚሆንለዎት አንጠራጠርም ።

ብርሃን ተድላ

## ዜና ሊቃውንት

### የአለቃ ሺዋጋህ አሰማኸኝ አጭር የሕይወት ታሪክ

አለቃ ሺዋጋህ አሰማኸኝ በጐንደር ክ/ሀገር በደብረታቦር አውራጃ ፋርጣ ወረዳ ልዩ ስሙ ቅስና ጥ እስጢፋኖስ ከሚባለው ደብር ከአባታቸው ከሙሉጌታ አሰማኸኝና ከእናታቸው ከወ/ሮ የኋላዬ መስከረም ፳ ቀን ፲፰፻፹፰ዓ.ም ተወለዱ ።

እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የዚሁ ደብር መምህር ከነበሩት ከመምህር ገ/ማርያም ትምህርታቸውን ጀምረው ንባብ ፣ ጾመድጓና ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

፩ኛ/ ማህደረ ማርያም ከመምህር ገ/መድህን ቅኔ ተቀኝተዋል

፪ኛ/ የቅኔ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ዋህር እስጢፋኖስ ስመጥር ከነበሩት ከመምህር ፀቃውዕ ለሁለተኛ ጊዜ ተቀኝተዋል

፫ኛ/ ፍትሐ ኢየሱስ ከነበሩት ከመምህር ቢወጣ ዝማሬ መሥዋዕት እስከመምህርነት ደረጃ ከተማሩ በኋላ የዜማ ትምህርታቸውን ለማስፋፋት ማህደረ ማርያም ስመጥሩ ከነበሩት ከቅስና ጥ ወርቁ ድጓ ተምረዋል ።

፬ኛ/በወገራ አውራጃ ደቋ ኪዳነምህረት የዚሁ ደብር ተወላጅ ከነበሩት ከመምህር ፈንታ ለሁለተኛ ጊዜ ድጓ ከተማሩ በኋላ ወደ ትውልድ አገራቸው ተመልሰው በጋይንት አውራጃ አቃቤት ማርያም ከነበሩት ከመምህር ያለው የድጓ ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ በዚሁ አውራጃ ውስጥ የድጓ ማስመስከሪያ ከሆነችው ስመጥር ቤተ ልሂም ወርደው /ከአለቃ/ መርሻ ለ፰ ዓመት ያህል ድጓ በመማር ልክ እንደዘመኑ ዩኒቨርስቲ ወግና ማዕረግ ባለው ስነስርዓት ተመርቀው የሊቅነት ምስክርነታቸውን ከመምህሩ ተቀብለዋል ።

አለቃ ሺዋጋህ አሰማኸኝ ለመንፈሳዊ ትምህርት የነበራቸው ፍላጎት ከፍተኛ ስለነበረ በዚሁ ሳይወሰኑ የጐንደርን የመረግድ ቀለም ለመማር ወደሰቆጣ ሄደው የጐንደርን የመረግድ ቀለም ከሚያውቁት ሊቃውንት መካከል በ፩ኛ ደረጃ ይታወቁ ከነበሩት ከአለቃ አለሙ ከበሴ የጐንደርን የመረግድ ቀለም ለ፯ ዓመታት ያህል በመማር በመምህርነት ተመርቀዋል ይሁን እንጂ ሰቆጣም በነበሩበት ዘመን የደብሩ አስተዳዳሪ ከነበሩት ከመምህር ማህፀንቱ በቀኝ ጌትነት ማዕረግ ካባና ቀሚስ ተሸልመዋል እንዲሁም ከሰቆጣ ገበያ በቀረጥ የሚገኘውን ያሊቃውንና የማህበሩን አበል በኃላፊነት በመረከብ ለደብሩ አስተዳዳሪና ለማህበሩ አበላቸውን ያስረክቡ ነበር አለቃ ሽህዋጋህ ከመምህር አለሙ ከበሴ ደቀመዛሙርት መካከል

፩ኛ/ በግብረ ገብነት

፪ኛ/ በውቀት ተወዳዳሪ ያልነበራቸው ምሑር ስለነበሩ በዋግሺም ከበደ የስዕል ቤት እየተገኙ

፩ኛ/ ከደብሩ አስተዳዳሪ መምህር ማህፀንቱ

፪ኛ/ ከአለቃ አለሙ

፫ኛ/ከቅኔው መምህር ገብረ ማርያም ጋር በመሆን ጸሎት ያስታኩቱ ስለ ነበረ ከዋግሹም ከበደ ዘንድ

፩ኛ/ ካባና ቀሚስ

፪ኛ/ ለ፰ ጊዜ ሙሉ ልብስ ተሸልመዋል

በ፲፱፻፲ ዓ.ም. ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ጎንደር ተመልሰው በዚሁ የትውልድ አገራቸው ቅስናጥ እስጢፋኖስ በመምህርነት ተሹመዋል ።

፩ኛ/ አቋቋም

፪ኛ/ፀዋትወ ዜማ እያስተማሩ ከ፶ በላይ ተማሪዎችን አስተምረው በመምህርነት አስመርቀዋል ። ለምሳሌ ከአስተማሩአቸውም ምሑራን መካከል

፩ኛ/ መምህር እንግዳ ወርቅ

፪ኛ/ መምህር ገሠሠ ብሩ ዳውንት ጉድባ ጊዮርጊስ

፫ኛ/ መምህር መንግሥቱ ትግራይ ክ/ሃገር

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# አዲስ የታሪክ ምዕራፍ

እንደ እጥቢያ ኮከብ የሚያበራ ሕያው ታሪክ ያለውን የታላቁን ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድን የዜማ ድርሰት የትርጉምና የቅኔ ጥበብ በሰብአዊ ቋንቋ ለመግለጥ ብንሞክር የፀሐይን ብሩህነት ለማስተዋወቅ የሻማ መብራት ይዞ እንደመውጣት የሚቆጠር መሆኑ ይሰማናል ። ስለምን ? ቢባል የዚህ ሊቅ ሙያና ተግባር ሁሉ ከሰብአዊ አእምሮ በላይ በመሆኑ ታሪኩን ለመግለጥ የሰብአዊ ቋንቋ ቃላት ብቃት አይኖራቸውም ።

ዳሩ ምን ይሆናል "በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ቁጥር ነው" እንዲሉ ይህ ሊቅ ደሙ ከደማችን አጥንቱ ከአጥንታችን የተዋሐደ የራሳችን ተወላጅ መሆኑ እየታወቀ ትምህርቱን ብሔራዊ ቅርስ አድርገን ወርሰን እየተጠቀምንበት ሳለ በቤተ ክርስቲያናችን በቂ መታሰቢያ ሳይቆምለትና የሚገባውንም ያህል ከዓለም ኅብረተሰብ ጋር ታሪኩን ሳናስተዋውቅለት በመቆየታችን አባቶቻችንም እኛም በታሪክ ፊት ተወቃሾች ከመሆን አናመልጥም ።

የሠለጠነው ዓለም ኅብረተሰብ ከመካከሉ የተነሡትን ታናናሽ ሊቃውንት እንኳ ሳይቀሩ ታሪካቸውን እያጐላ ልዩ ልዩ መታሰቢያ በማቆም ስማቸው ከደመና በላይ ሆኖ ዝናቸው በየአህጉሩ ገንኖ ሲነገርላቸው ያሬድን የመሰለ ማኅሌታዊ የዜማ ደራሲ ፣ የቅኔ ጥበብና የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቅ ቤተ ክርስቲያን ልትዘነጋው አይገባም ።

በየዓመቱ ግንቦት 11 ቀን በሚዜምለት ድጓው "በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከርሱ በፊትም ሆነ ከርሱ በኋላ ያሬድን የመሰለና እርሱን ያክል ዜማዊ ሰው አልተነሣም እርሱ የክርስቶስን ትንሣኤ ይሰብካል ፣ ሰው ብቻ ሳይሆን እንስሳትና አዕዋፍም እንኳ በደመ ነፍስ ቋንቋቸው (ኢንስቲንክት) የሚያሰሙት ዜማ ከሦስቱ የያሬድ ዜማዎች ማለትም ከግዕዝ ፣ ዕዝልና አራራይ ውጭ መሆን አይችልም" ተብሎ በጥንት ሊቃውንት የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ምስክርነት የተሰጠለት ይህ ሊቅ የታሪኩ ግዙፍነትና ምልአት ስፋቱ በመላው ዓለም ታሪካቸው ከተንሰራፋው ሊቃውንት በምን እንሶ ይህን ያህል እንደተዘነጋ ስናስብ በቂ ምክንያት ለመስጠት ካለመቻላችን የተነሣ ለኅሊናችን ብርቱ ጭንቀት አይሰማውም እንዴ !

እረ ለመሆኑ ይህ ታላቅ ሊቅ ከተነሣበት ዘመን ጀምሮ ለ፩ሺ፬፻ ዓመታት ያህል በተከታታይ በየዘመኑ በተነሣው ትውልድ መካከል ከነበሩትና ዛሬ በሞት ደመና ከተሸፈኑ ዕልፍ አዕላፍ ሊቃውንት ካህናት ወይም አሁን ካሉት ብዛታቸው ወደ ፪፻ሺ በላይ ከሆኑት ካህናት መካከል አንድ እንኳ ከቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ያልቀሰመ ይገኛልን ?

በኅብረተሰቡስ መካከል ከከተማ እስከ ገጠር ሲተም በሚኖረው ሙዚቃና ዘፈን ቀረርቶና ሆታስ ወይም በኃዘን እንጉርጉሮውና ሙሾው ወይስ በታቦት ዘፈኑ (ወዘተ) የቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ያልተቀላቀለበት ምን ዓይነት ዜማ ይገኛል ? እንግዲያውስ ቅ/ ያሬድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ባለውለታ ነው ። የሚገባውን ያህል ብናስተዋውቀው ኖሮ የመላው ጥቁር ሕዝብ መዲና የሆነችውን አፍሪቃን የሚያኮራ ታሪካዊ ምስክር ለመሆን በበቃ ነበር ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የጸጋው ዘመን ገና አላለፈምና ከእንግዲህ ወዲህም በብርቱ ከታሰበበት ከታለመው ግብ መድረስ የሚቻልበት ጐዳና ተከፍቷል። ይኸውም ኅዳር ፳ ፻፸፭ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገኙበት በተከበረው ታላቅ በዓል ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ከቤተ ክህነቱም የመምሪያ ኃላፊዎች ከገዳማት አስተዳዳሪዎችና ከአድባራት አለቆች በርከት ያሉት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምዕመናን ከአጥቢያው ሕዝበ ክርስቲያን ጋር የተካፈሉበት ታላቅ ጉባኤ ሆኖ በሙዋሉ ደብረ ይባቤ በሚል ሥያሜ በመቃኞ የቆየውን የቅ/ ያሬድን ቤተ ክርስቲያን ለማሳነፅ የሚያስችል የገንዘብና የማቴሪያል እርዳታ ለማድረግ የታየው ርብርብና እሽቅድድም እስካሁንም አስታዋሽ በመታጣቱ እንጂ ለካስ ይህ ሊቅ ዕልፍ አዕላፍ ወዳጆች አሉት" የሚያሠኝ ሆኖ አግኝተነዋል ።

በዚሁ በዓል ላይ ትምህርት እንዲሰጡ ከተጋበዙት ሊቃውንት መካከል አለቃ አያሌው ታምሩ የዚህን ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅ/ያሬድ ዜና ሕይወትና ጣዕመ ዜማውን ከጽ፬ቱ ካህናተ ሰማይ ከሱራፌል ተካፍሎ ያመጣው መሆኑን ይህን ሊቅ በደራሲነት በትርጉም ሙያውና በቅኔው ከሊቃውንት ሁሉ ቅድስናውም ከመላእክት ጋር በማገናኘት ልብ የሚነካ ምስክርነት ሰጥተውለታል በቂ መታሰቢያ ሳይቆምለት እስካሁን የመቆየቱንም ፀፀት አሚልተው አስፍተው በመግለጥ ያለፈው ዝንጋኤ እንዳይደገም በማክበር አሳስበዋል ።

መምህር ሰሎሞን ገ/ሥላሴም የዚህን ታላቅ ሊቅ ባለውለታነት የሚገልጥ ሰፊ ትምህርት ከመስጠታቸውም በላይ የበዓሉ ተካፋዮች የሆኑ ሁሉ የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉ በማሳሰብና በማስተባበር ረገድ ያልተቆጠበ ትጋት አሳይተዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በሰጡት ቃለ ምዕዳን የዚህ ታላቅ ሊቅ መታሰቢያ የሚሆን ቤተ እግዚአብሔር በማሳነፅ ብቻ ሳይወሰኑ መዘምራን ሊቃውንት የሚበዙበት የልዩ ልዩ ፀዋትወ ዜማ ት/ቤትም አብሮ እንዲሠራ ያላቸውን ዕቅድ በመግለጥ ለጊዜው ቤተ ክርስቲያኑ ካላት ገቢ አሥር ሺህ ብር እንዲሰጥ ከመፍቀዳቸውም በላይ ወደፊት የመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ልግስና የማይለየው መሆኑን በማብሠር የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ የተጣለበትን አደራ ከፍጻሜ ለማድረስ ያልተቆጠበ ትጋት እንዲኖረው አሳስበዋል ።

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ይህ የቅ/ያሬድ መታሰቢያ ቤተ እግዚአብሔርና ት/ቤት በዘመናዊ እቅድ የመሠራቱ እንቅስቃሴ አንድ አዲስ ምዕራፍ በመሆኑም አኩሪነቱ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለአፍሪቃም ጭምር ነው ። ስለዚህም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተ/ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የዚህ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፋች ለመሆን ወሥነው መነሣታቸው ከዚህ በፊት ከነበሩትም ሆነ ወደፊት ከሚነሡት መንፈሳውያን መሪዎች የተለዩ ዕድለኛ የሚያደርጋቸው በቂ ምክንያት ያለው ታላቅ አጀማመር መሆኑን የሚጠቁም ብሩህ ተስፋ አሳይቷል ።

እኛስ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን ካህናት ይህ አበ ብዙኃን ሊቀ ሊቃውንት ቅ/ያሬድ በቤተ ክርስቲያን ስም ለመላው ሕዝባችን ጭምር ላስገኘው ታላቅ በረከት ሙሉ ወረታ መክፈል ባንችልም እንኳ በስሙ ለሚሠራለት ቤተ እግዚአብሔርና የፀዋትወ ዜማ ት/ቤት የሚኖረን የአስተዋፅዖ ድርሻና ተሳትፎ ምንድን ነው ? "ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይረዳም" እንዲሉ አንዱ ዋና ተግባራችን የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ምዕመናንን ማሳሰብና ማስተባበር ሲሆን ልግስናውም ከእኛ መጀመር ሲገባው የሚጠበቅብንን ትጋት አለማሳየታችን በታሪክ ፊት ተወቃሾች እንዳያደርገን ልናስብበት ይገባል "ብፁዕ ዘይሁብ እምዘይነሥእ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" ተብሎ እንደተጻፈ መታሰቢያነቱ ቅ/ያሬድ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኑ የቅዱስ አምላካችን መመስገኛ ት/ቤቱም የእኛውና የልጆቻችን መማሪያ ስለሆነ የራሳችንን ቤት እንደምንሠራ ያህል ሆኖ መቆጠር አለበት ። የቅ/ያሬድ የዜማ ድርሰት ስብሐተ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የካህናትም መተዳደሪያም ሀብት (በጀት) ነው ለማለት ያስደፍራል ። ከጥንት ጀምሮ የምዕመናን ሰፊ ልግስና ለቤተ ክርስቲያን ሲጐርፍላት የሚኖረው በእንግዲያውስ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ "አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀው አባት ያላቆየው ለልጅም አይበጅው" ሲሉ እንደተናገሩ ዛሬ እኛ ያልመሠረት ነውና ያላቋቋምነው ምንም ነገር ለትርሱ ጣዕመ ዜማ ከሚገኘው የመንፈስ ተሐድሶ ነው ። ውዳሴው ቅዳሴው ፣ ጠቅላላ ማኅሌታዊ አገልግሎቱ ሁሉ ያለቅዱስ ያሬድ ዜማ ይቅረብ ቢባል ደረቅ ንባብ ብቻ ሆኖ ከመቅረት አይዘልም ። ውልደ ትውልድ ተወራሽ መሆን እንደማይችል ተገንዝበን ይህን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተጋግዘን ከግቡ ለማድረስ እንትጋ ።

ቄ/ መክብብ አጥናው



« ወደ ተራራ ውጡ እንጨቱንም አምጡ ቤቱንም ሥሩ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል ።»

ሐጌ ም/፩ ቁ ፰ ።

## ደስታ

ከገፅ ፳፮ የዞረ

ታ ይለቅማሉ በሄዱም ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶዋቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመለሳሉ ብኋል መዝ ፻፳፭/፻፳፮/፭

ሥጋዊ ደስታም የሚጠላ ነው ማለታችን አይደለም ሥጋዊ ደስታም ሕብረተሰቡን የሚጠቅምና ከመንፈሳዊ ደስታ ጋር አንድ ሆኖ የሚሄድ ከሆነ መልካም ነው ክርስቶስ እንድንድንእንጂ በሐዘን እንድንኖር ፈቃዱ አይደለምና ።

ከነፈርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

በግብርና በረከት ለመጠቀምና ሌላውንም ለመጥቀም ፣ ኃይልን አስተባብሮና ከባለሙያዎች ጋር ተመካክሮ መሥራት ያሻል ።

ከዚህም ጋር አስደሳች ውጤት ለማግኘት በተሰለፉት በዚሁ የእርሻ መስክ ላይ በትጋት ማረስና መቆፈር ፣ ከባለሙያዎች የሚሰጡትን መምሪያዎች በሥራ መተርጐም የበለጠ የግብርና በረከትን ለማትረፍረፍ ይቻላል ።

የግብርና በረከት ጥቅም ቀደም ሲል የታወቀ ዛሬም ጥቅሙ የበለጠ የገነነና ለወደፊትም የሚኖር ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ ስለግብርና በረከት ለቀደሙት ሰዎች ያስተላለፈው መመሪያ በታላቁ መጽሐፍ በብዙ ቦታ ተመዝግቦ ይገኛል በኦሪት ዘፍጥረትም ዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፱ ላይ "እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዝሩ ፣ በርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ የዛፍንም ፍሬ የሚያፈራውንምዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁናችሁ" ይላል እዎ በዚህ አምላካዊ ትእዛዝና መመሪያ መሠረት የሰው ልጅ ለመብላት ፣ መሥራት ፣ በመሥራትም መብላትና በውጤቱ መደሰትም እንዳለበት ተገንዝቦ ከሥራዎች ሁሉ የግብርናን ሙያ ቅድሚያ ሰጥቶታል ፣ በዚህም ሙያ የግብርናን በረከት ለማግኘት የድካሙን ፍሬ ለመረከብ ከአሮጌው የእርሻ ዘዴ ወደ አዲሱ ሳይንሳዊ የአስተራረስ ዘዴ እየተሸጋገረ ይገኛል ይኸም ውጤት የሚኖረው "አንድነት ኃይል ነው" የሚለው ቃል በኅብረት ሥራ ሲጠናከር መሆኑን አምኖ ዛሬ በዚህ ተግባር ላይ እየተረባረበ ይገኛል ።

እንደገናም እግዚአብሔር ይህን የግብርና ሙያ ከሁሉ በላይ ተመልክቶ የመጀመሪያውን ሰው ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው በማለት ያብራራል ዘፍ.፪.ቁ.፲፭።

እንግዲህ ያለንባትን ምድር በእርሻ በሌላም ሌላ እንጠቀምባት ዘንድ ከጠበቅናትና ካበጃጀናት የሰጧትን አደራ ሳታበላሽ ከነጥቅሙ ትሰጠናለች ፣ እስከአሁን ከአየናቸው ሁሉ አደራዋን ጠብቃ የምታስረክብ ምድር ብቻ ናትና ።

ከጠበቅናትና ካበጃጀናት ስንል በተፈጥሮ ጉርፍ ተቆራርሳና ተንዳ እንዳታልቅ በውስጧ ያሉ አያሌ ጅረቶች ያለ ጥቅም ባዝነው እንዳይቀሩ ታላቁና የኢትዮጵያ እናት የሆነው አዋሽ ወንዝ የሚሰጠውን በረከት እነዚያም እንዲሰጡ መጣጣር ማለታችን ነው ።

በዚህ መንገድ ምድርን ካበጀናትና ከጠበቅናት ካረስናትና ከአለሰለስናት የምንሰጣትን ዘር ተቀብላ አበርክታ ትሰጠናለች ይህ በመሆኑም በሚገኘው ምርት ተጠቅመን ሌሎችንም ለመጥቀም ስንችል አገራችንም በምርት እድገት በልጽጋ ሌሎች በልማት ከበለጸጉ አገሮች ጐን ልትሰለፍ ትችላለች ።

ይህን ዓይነቱን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር የሚሰጠውን መመሪያ ዕለት በዕለት በመቀበል እንደመመሪያው ለመጠቀም ሲቻል ነው ።



ዘመናዊ የእርሻ መኪና

በአሁኑ ወቅት የግብርና ሥራ ከዕለት ወደ ዕለት ዘመናዊ አሠራር እየተለወጠ በመሔድ በጓሮ አትክልት እንኳ ጠቀሚ የምርት ውጤት እየታየ ነው በዚያም በዚህ የእርሻ ሥራ እያደገ ከሔደ አገራችን በቅርብ ጊዜ ምድረ ገነት እንደ ምትሆን እሙን ነው ።

በየወሩ እየታተመ የሚወጣው "ዜና ግብርና" ቁጥር ፩ ቅጽ.፩ መስከረም 1975 ዓ.ም ከወጡት ዜናዎች ገጽ ፲፯ ላይ በጐንደር ክፍለ ሀገር በሊቦ አውራጃ በአዲስ ዘመን ከተማ በአንድ ሔክታር መሬት ላይ የተከናወኑትን የአትክልትና የፍራ ፍሬ ውጤቶች ተንትኖአል እኛም ይህንኑ ውጤት ዜናው ላልደረሳቸው ለማዳረስ ፣ ላላወቁ ለማሳወቅ ከዚህ እንደሚከተለው ፍሬ ነገሩን ወስደነዋል ።

ከመጽሔቱ የተወሰደው ሙሉ ቃል "በአንድ ሔክታር መሬት ላይ የ፳፪ ዓይነት ያትክልትና ፍራፍሬ የሠርቶ ማሳያ ጣቢያ በግብርና ሚኒስቴር ተጀምሮ አስደሳች ውጤት በመስጠት ላይ ነው ።

ይህ በግብርና ሚኒስቴር ባለሙያዎች የአትክልትና ፍራፍሬ ሠርቶ ማሳያ የሚከናወነው የዘር ዓይነት ቆስጣ ፣ ሙዝ ፣ ሽንኩርት ፣ ኮክ ፣ ሱካርድንች ፣ ሽንኮራ አገዳ ፣ ፓፓያ ፣ ትርንጐ ፣ ሎሚ ሲሆኑ 12 ዓይነት ያላቸው የቲማቲም ዘሮችም ይገኛሉ መጽሔቱ እነዚህን ዘሮች በዚያ ቦታ ለማልማት የአካባቢው አየር ተስማሚ በመሆኑ በተደረገው ሙከራ አጥጋቢ ውጤት መገኘቱን አብራርቶአል ።



እነዚህ የዘር ዓይነቶች በሙሉ ከውጭ አገር መጥተው በሙከራ ላይ የነበሩ ሲሆን በምርጥ ዘርነታቸው ጠቃሚነት ያላቸው መሆናቸውን የጣቢያው ባለሙያ ያስረዳ መሆኑን መጽሔቱ ጠቁሞአል ።

ከዚህ ጋር እነዚህን የዘር ዓይነቶች በበለጠ ለማስፋፋት በአካባቢው ለሚገኙ ያምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በማከፋፈል በጓሮ አትክልት ሥራ እንዲጠቀሙበት እየተደረገ አጥጋቢ ውጤት ተገኝቶአል ።

እጅግ በጣም የሚያስደስተው ደግሞ በዚሁ ቦታ የሩዝ ችግኝ በግሩም ሁኔታ ሊለማ እንደሚችል መጽሔቱ በሚከተለው ዓይነት ያብራራዋል ።

በሩብ ሔክታር ላይ ከሚገኘው የሩዝ ችግኝ 10 ሔክታር ለማልማት እንደሚቻል አባላቱ አስረድተዋል ፣ ከዚህም በስተቀር ሥራውን ለማስፋፋትና ይህን የሩዝ ምርት ከፍ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከግብርና ሚኒስቴር የአፈርና የውሃ ልማት መምሪያ ፪ የውሃ መሳቢያ ሞተር ሰጥቶአል ።

ስለሩዝ ካነሳን ዘንድ በገጽ 19 ላይ ስለሩዝ ልማት እንደሚከተለው ይተነትነዋል የሩዝ ዘር ምርት የሚሰጠው ከ፩፻፴-፩፻፶ ቀናቶች ሲሆን አሠራሩ ችግኙን በመትከል ነው ። ይህ ዘር በዓመት ፪ ጊዜ ምርት እንደሚያስገኝና ዛሬ በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምርት ለገበያ መብቃቱ በመጽሔቱ ተገልጾአል ።

እንግዲህ የግብርና ሙያ ከተጠናከረ በዓለም ላይ አሉ የሚባሉ የእህልና የአትክልት ዓይነቶች በአገራችን የበለጠ እንደሚለሙ ከዚህ ይዞታ እንረዳለን ።

በአንዳንድ ቦታ በጓሮ አትክልት የሚጠቀሙ ትጉሃንም የቦታውን ተስማሚነት ለባለሙያዎች በማሳወቅ በምርት ውጤት ራሳቸውን ለማስደሰት ይችላሉ ።

እግዚአብሔር የሰው ልጅ በኑሮው ተደስቶ ይኖር ዘንድ ከሰጠው ፀጋና በረከት ከምድር የሚያገኘው በረከት አንደኛውና የመጀመሪያው ነው ።

ስለዚህ የግብርና በረከት ለሁሉም እንዲደርስና አዲሱም የሙያ አሠራር በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ ከግብርና ሚኒስቴር የእርሻ ባለሙያዎች ጋር መመካከር አስፈላጊ መሆኑን ለማወቅ ይቻል ዘንድ ይህን መልእክት እናስተላልፋለን ።

በለጠ አበበ

## የአለቃ ሺዋጋህ...

ከ፲፩ ገፅ የዞረ

፩ኛ/ አለቃ ምህረት ሸዋ ክ/ሃገር የመናገሻ ማርቆስ አስተዳዳሪ

፪ኛ/ አጋፋሪ እስጢፋኖስ ሸዋ ክ/ሃገር የመናገሻ ጊዮርጊስ

፫ኛ/ ግራዝማች ተገኝ ጐጃም ክ/ሃገር ይገኙባቸዋል ።

አለቃ አለሙ ከበሴ የጎንደርን የመረግድ ቀለም ለደቀ መዛሙርቶቻቸው ሲአስተምሩ የነበሩት

፩ኛ/ የባታን

፪ኛ/ የላይ ቤትን

፫ኛ/ የስንኳን ቀለም በአንድ ላይ በማቀነባበር ስለነበረ በጎንደር ሊቃውንት ዘንድ የሰቆጣ ቀለም የሚል ትችትን ከማስከተሉ የተነሣ በአለቃ ዓለሙና በጎንደር ሊቃውንት ደቀ መዛሙርት መካከል በየጊዜው መለያየትን ያስከትል ነበር ። ነገር ግን አለቃ ሺዋጋህ ጉባኤ ዘርግተው በሚያስተምሩበት ዘመን ፩ኛ. ቆሮ ም. ፩ ቁ ፲-፲፩ ያለውን መንፈሳዊ የምክር ቃል በተግባር ለመተርጐም ከላይ ፩-፫ ተራ ቁጥር የተጠቀሱትን የጐንደር የመረግድ ቀለሞች በየቤታቸው እንዲባሉ ለደቀመዛሙርቶቻቸው በማስተማር ከላይ በተጠቀሱት ምሑራን መካከል አንድነት እንዲፈጠር ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ መንፈሳዊ ምሑር ነበሩ ።

ይሁን እንጂ በዚህም የትውልድ አገራቸው ሲያስተምሩ በነበሩበት ዘመን ወሎ ክ/ሃገር ከቀድሞ አልጋ ወራሽ ፣


፩ኛ/ ካባና ቀሚስ

፪ኛ/ ካባ

፫ኛ/ የዚሁ ደብር አስተዳዳሪ ከነበሩት ከመምህር ወልደጊዮርጊስ ካባና ቀሚስ ተሸልመዋል ።

፬ኛ/ የዚሁ ደብር አስተዳዳሪ ከነበሩት ከአለቃ ደስታ ወልዱ ዘንድ ካባና ቀሚስ ተሸልመዋል ። እንዲሁም ፩ኛ . ከ፲፱፻፵፫-፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ድረስ በደብረ ታቦር አውራጃ በፎገራ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የቋህር ቅዱስ ሚካኤልን ደብር ከ፲፱፻፶፩-፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ከዚህ አለም በሞት እስከ× ተለዩበት ዘመን ድረስ የትውልድ አገራቸው የሆነውን የቅስጥና እስጢፋኖስ ደብር በእልቅና ሲአስተዳደሩ ኑረዋል ።

ይሁን እንጂ አለቃ ሺዋጋህ እምነትህን በሥራህ አሳየኝ የሚለውን መንፈሳዊ



አለቃ ሺዋጋህ አሰማሽኝ እኒህ ነበሩ

ቃል በመከተል የቅስናጥ እስጢፋኖስ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ በሚሠራበት ዘመን ከገንዘብ እጥረት የተነሣ ሥራው እንዳይቆም በማሰብ ከ፲፱፻፶፱-፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ድረስ ያለውን ደመወዛቸውን /በጥሬ ገንዘብ ብር ፬ሺ ፪፻፶፮/ አራት ሺ ሁለት መቶ አምሣ ስድስት/ የሆነ ለቤተክርስቲያኑ ህንፃ ሥራ እንዲሆን የለገሱ መንፈሳዊ አባት ነበሩ ።

እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በ፩ኛ ጢሞቴዎስ ም.፬ቁ.፲፪ ላይ በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናምለ

ወደ ገፅ ፲፱ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ

(በከፍያለው መራሂ)

## ሥርዓተ ጋብቻዎ በተክሊል እንዲሆን ልዎ ይወዳሉ?

እንግዲያውስ ስለ ሥርዓተ ተክሊል ማወቅና መረዳት ፡ እንደዚሁም ከጸሎተ ተክሊሉ ጋር አብረው የሚሄዱ ነገሮችንም ጭምር ጠንቅቆ ማስተዋል ይኖርብዎታል ። ተክሊል ማለት ክብር ሲሆን ፡ ሥርዓተ ተክሊል ማለትም የቃል ኪዳን ሥርዓት ማለት ነው ። አንድ ወንድ በአንዲት ሴት መጽናት የወንጌል ሕግ ስለሆነ ፡ "ወፈረች ፡ ቀጠነች ፡ መከነች ብዬ አልፈታትም" ሲል በካህኑና በቤተ ክርስቲያን ፊት ቃለ መሐላ ይፈጽማል ። እሷም "በችግሩ ሁሉ እረዳዋለሁ" ስትል ቃል ትገባለች ። ከሥነ- ፍጥረት ታሪክ እንደምንረዳው አንድ አዳምን ፈጥሮ ፡ ሁለት ከሴቶች ቢፈጥር ኖሮ ዛሬ ሁለት ማግባት በተቻለ ነበር ። ነገር ግን ለአንዱ የመጀመሪያው ሰው ትረዳው ዘንድ አንዲት ሴት ብቻ ነው የፈረሰው ። ስለዚህ ሰው አባት እናቱን ትቶ የሚስቱን ፈቃድ ይከተላል ፡ ሁለቱም በግብር አንድ ይሆናሉ ይላል ። በዚህ ዓለም ሳሉ በሕግ አግብተው እሥራት በኩራት አውጥተው ሥጋውን ደሙን በሚገባ ተቀብለው ቢኖሩ በመንግሥተ ሰማይም አንድ ዓለም ወርሰው ይኖራሉ ። ስለዚህም ባልና ሚስት አንድ አካል እንጅ ሁለት አይባሉም ። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውምና ።

አያሌ ክርስቲያን ወጣቶች ሥርዓተ ጋብቻቸው በተክሊል እንዲከናወንላቸው ይወዳሉ ። ነገር ግን ተክሊል ሲባል ለፎቶግራፍ ብቻ አለመሆኑንና በክርስትና ሕይወት ታላቅ ምሥጢር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። አንድ ጊዜ በአንድ ትልቅ ዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ እጀቢ ሕዝብ የተገኘበት ሥርዓተ ተክሊል ሲደርስ አጋጠመኝና ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ሥርዓቱን ስከታተል ፡ ብዙ ዝግጅት ነበረበት ፡ ካሜራውና ፊልሙ በእየደቂቃው ብልጭ ድርግም ይላል ፡ ነጭም ጥቁሩም የተጋበዘው ሕዝብ ነበር። ሕጉ፣ ሥርዓቱና ቃለ መሐላው ከተፈጸመ በኋላ ያለ ቅዱስ ቁርባን ሲሰናበቱ በማየቴ ነገሩ አሳዘነኝና ከእጠገቤ ለነበሩት አዛውንት ዘወር ብየ ከዚህ የሚቀጥለውን አስተያየት ሰነዘርኩ ፦ የእኔ አባት ሥርዓቱ እጅግ ያማረ ነበር "የሺህ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ" እንዲሉ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ማሠሪያው ቅዱስ ቁርባን ስለሆነ ያለ አንዳች እልባት ተለያየን ብላቸው ፡ አዛውንቱ እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ ፦ "አየ ልጄ! ኧረ ይሄስ የተሻለ ነው የዛሬ ዘመን ልጆች መተጫጫው ፒያሳ ጋብቻው ገፈርሳ" አይደለምን? አሉኝ ።

በእርግጥ ለተክሊል ሥነ-ሥርዓት የመጡት እነዚያ ሙሽሮች አምላክ ጋብቻቸውን እንዲባርክላቸው ፣ጸሎት እንዲደረስላቸው በነገሩ አምነውበት የመጡ ከሆኑም የተሻለ ነው ፡ ቅዱስ ቁርባንን ገንጥሎ ማየቱ ካለማወቅና ካለመረዳት ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ለፎቶግራፍና ሥነ ሥርዓቱን ማሳመር የመጡ ከሆነ እጅግ ታላቅ ስህተት ነው ። ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን አትደግፈውም ። እያንዳንዱ ክርስቲያን ከጋብቻ በፊት ሊያውቅ የሚገባው ነገር ቢኖር "አንድ ወንድ ላንዲት ሴት" የሚለውን የጌታ ትእዛዝ ማስተዋል ነው ፡ አንድ ክርስቲያን ይህ ትእዛዝ መኖሩን ካወቀ ተክሊልን ከቅዱስ ቁርባን ገንጥሎ ሊያየውና ከቅዱስ ቁርባንም ሊያሸሸው አይችልም ፡ ምክንያቱም ራሱን ባንዲት ሚስት እንዲገታ ፡ ራሱን እንዲቆጣጠር የሚያደርገው ከቅዱስ ቁርባንም በፊት አንድ ትእዛዝ አለና ነው ፡ ይኸውም በድጋሚ "አንድ ወንድ ላንዲት ሴት ፡ አንዲት ሴት ላንድ ወንድ" የሚለው ነው ፡ ይህ ትእዛዝ እንግዲህ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ልጓም ሊሆነው ይገባል ።

"ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም" እንዲሉ ወጣቶች ከጋብቻ በፊት የትዳር ጓደኞቻቸውን እንዴት መምረጥ እንዳለባቸውና ስለጋብቻ ቅድስናትምህርትያስፈልጋቸዋል ። "እኔና አንቺ ከተዋደድን" ከሚል ጭፍን አስተሳሰብ ትዳር ከተመሠረተ በኋላ መጨበጫው ሲጠፋ ፡ "ምነው የተገናኘን ዕለት በሞትኩት" ማለት ይመጣል ። ስለ ጋብቻ መሠረታዊ ዓላማዎች ስናስብ የመጀመሪያው ፈቃድ ዘር መተካት ወይም መራባት ሲሆን ፡ ለቀደሙ አያቶች ብዙ ተባዙ ያላቸው የእግዚአብሔር ቃል ወደዚህ ይመራል (ዘፍ፩ ፡ ፳፰) ይህም ትእዛዝ ያለሩካቤ አይፈጸምም ። በእርግጥ ሩካቤ ሥጋ ከጋብቻ አንደኛውና ትልቁ ክፍል ቢሆንም ጋብቻ ከሩካቤ ሥጋ የሚበልጥ ሌላ ጥልቅ የአንድነት ምሥጢር አለበት ፡ እውነተኛ ፍቅር ፡ በጐ መተሳሰብና መከባበር ወዘተ .. ነው ።

ሁለተኛው ትእዛዝ በተጋቡት ወጣቶች መካከል በዚህ ዓለም ድካም ለማቅለል አንዱ ለአንዱ የሚያደርገው መረዳዳት ነው ። ልዑል እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰው ጓደኛ እንፍጠርለት እንጅ ብቻውን ሊሆን አይገባም ብሎ የተናገረው ቃል ወደዚህ ይመራል ፥ (ዘፍ.፪ ፡ ፲፰) ስለዚህም ጋብቻ አስፈላጊ የሆነበት ተቀዳሚው ተግባር ልጅን ለመውለድ ፡ ፍትወትን ለማራቅ ለመረዳዳትና አንድ ለመሆን ነው ። ይህም አስቀድሞ በተነገረው በኦሪቱ ሥርዓት (ዘፍ.፪ ፡ ፳፬) ዳግመኛውም በሁለተኛው ዘመን በተነገረው በወንጌል ሥርዓት (ማቴ.፲፱ ፡ ፭ ተረጋግጧል ።

# እርጅና

ከገፅ ፳ የዞረ

የቤተሰብ ሸክም አይደለም ። ልጆች ፡ የልጅ ልጆች እርሱ ያዘጋጃቸው ፍሬዎች ስለሆኑ አረጋዊ አባታቸውንና እናታቸውን መጦርና መንከባከብ ክብርና ሞገስ ነው ።

ሐዲስ ተረፈ



ስለዚህ በስነ - ሥርዓት ከተተከለ ዛፍ ጣፋጭ ፍሬ እንደሚጠበቅ ሁሉ ከመልካም ጋብቻም ለሃይማኖቱና ለታሪኩ ቀናተኛ ለሀገሩናለዳርድንበሩታማኝዜጋእንዲሆንይጠበቃል።ከወፍዘራሽ ተክል እጥጋቢ ፍሬ እንደማይሰጥም ሁሉ እንደዚሁም ከሥርዓት አልባ ጋብቻ ሞራሉ የተስተካከለ ፡ በሀገር ፍቅር የተቃጠለ ጨዋ ኅብረተሰብእ ለማግኘት ያዳግታል ። የኅብረተሰብእ ሳይንስ ሊቃውንትም ለማኅበራዊ ኑሮ መሠረቱ ከቤተሰብእ እያያዘ ጀምሮ መሆኑን ይናገራሉ ።

ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን ከሥርዓተ ጋብቻ ላይ መሠረታዊ የሃይማኖትና የሞራል ትምህርት ያስፈልጋል ብላ የምታስተምረው ፡ ምክንያቱም "አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው" እንዲሉ የወላጆች በስነ - ሥርዓት መኖር ለልጆች የፍቅርን ለዛና የማኅበራዊ ኑሮን ጣዕም በቀላሉ እንዲማሩና እንዲያውቁ ይረዳቸዋል ።

ስለዚህ አዲሱ ትውልድ ስለ ጋብቻ ጠለቅ ያለና መሠረታዊ አስተሳሰብ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። "መቀነቷን ትፍታውና ቢሆን ይሆናል ካልሆነ ትተወዋለች"የሚባለውም የልማድ አነጋገር ዛሬአይሠራም።የልማድተገኘ ከመሆን ይልቅ ያዋጣል እያዋጣም ብሎ በቅድሚያ ራስን መጠየቅ ፍቅር የሚያስከትላቸውን ሀላፊነቶች ለመሸከም ያስችላል ። አለበለዚያ ግን እውነተኛ መልክ የሌለው ፍቅር ፡ እንጀራ ሆኖ በመሶብ አይቀርብም ፡ ወደድኩሽ ወድጄሻለሁ የቤት ክራይ አይከፍልም ። በእውነተኛ ፍቅርና እምነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ በአለት ላይ በተመሠረተ ቤት ሊመስል ይችላል ፡ ጠንካራ መሠረት ስለሚኖረው በአሉባልታ ነፋስ በቀላሉ አይፈርስም ። በወረተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ጋብቻ ግን በድቡሽት ላይ በታነፀ ቤት ሊመስል ይችላል ፡ መሠረቱ ጥልቀት ስለሌለው በቀላሉ ይናወጻል ።

ስለዚህ ነው ወጣቶች አዲሱን የሕይወት ምዕራፍ ሲጀምሩ "የእንቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ" እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄና ማስተዋል ፡ ደጋግመውም እንዲያስቡበት የሚያስፈልገው። በእርግጥ ፍቅር ለጋብቻ አስፈላጊ መሆኑ የማይካድ ነው ፡ ስለሆነም ፍቅር በጋብቻ ክልል ውስጥ ሊሆን ይገባዋል ። ጋብቻ የፍቅር ሙዚቃ አብሮ እያደመጡ ቆንጆ ቆንጆ ልብስን ለብሶ ፡ እጅ ለእጅ ተያይዞ መንሸርሸር ብቻ አይደለም ። ጋብቻ የወር ወጭ ማውጣትን ፡ ምግብ ማብሰልን ፡ በሕጻናት ሽንት መጨማለቅን ፡ እንግዳ መሸኘትን ሁሉ ያጠቃልላል ። አንዳንድ ወጣት ወንዶች በጣም ቆንጆ የሆነች ፡ ሥራ ያላት የተማረችና ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ ያላት ቆንጆ ነው የምፈልገው" ይላሉ ። በልጃገረዶችም በኩል የሆነ እንደሆነ ብዙውን ጊዜ" ምን አለው? ቤት አለው? መኪና አለው? ደሞዙስ ጥሩ ነው ያኖረኛል? እኔንስ ማስጌጥ ይችላል ?...." በሚል በብልጭልጭ ነገሮች ላይ በማተኮር ፡ ለምርጫ ሲቀርቡ የሚገባቸውን ሁኔታ ካላማስተዋል በዚህ ላይ ትዳርን ለመመሥረት ይሞክራሉ ። በእርግጥ ማንም ሰው መልካም ነገር ለማግኘት ይመኛል ፡ ነገር ግን ርግብ እይዛለሁ ሲባል የሴት ወፍ መጨበጥ እንዳይሆን ጋብቻን ለመመሥረት ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ።

ስለዚህ ወጣቶች የትዳር ጓደኛቸውን ሲመርጡ ከውሳኔ በፊት ከሁሉ አስቀድመው አንዳንድ ስነ - ልቡናዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርባቸዋል ለምሳሌ ልጅቱ ሕይወቴን ልትተረጉምልኝ ትችላለችን ? ለትዳር ያላት አመለካከት ከአመለካከቴ ጋር አብሮ ይሄዳል? ጥያቄዎቹ ለሁለቱም ያታዎች ያገለግላሉ?።ጋብቻ በሁሉ የተከበረ ሊሆን ይገባል ። "መጋባት በሁሉ የከበረች ትሁን መኝታዋም ንጹህ ። ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል ።" ዕብ 13 ፡ 4 ። ስለዚህ ጋብቻ ቁምነገር ያለበት ነው እንጂ ቀላል ነገር አይደለም ። እንግዲህ ለማግባት የሚያስብ ሰው ሁሉ በጥንቃቄና በጸሎት እንጅ በችኮላ ባለማሰብ ሊያገባ አይገባውም ።

# እርጅና

የሰው ልጅ የመጨረሻ ዕድሜ ፸ ቢበዛም ፹ እንደሆነ በቅዱስ መጽሐፍ ተወስኖአል ። ከዚህ ካለፈ ግን ትቿፉ ፃርና ድካም ነው ይላል ። ይሁን እንጅ ኋላ ቀር ለሆኑት አገሮች ከዚህ ዕድሜ የሚደርሱት በጣም ጥቂት ናቸው ።

የሰው ዕድሜ ሕፃንነት ፡ ወጣትነት ፡ ጐልማሳነት አረጋዊነት ተብሎ በአራት ደረጃ ይከፈላል ። ሆኖም በተለያዩ ሁኔታዎች ብዙ ሰዎች ከአራተኛው ደረጃ ሳይደርሱ ከአንድ እስከ ሦስት ባሉት ደረጃዎች የሕይወት ዘመናቸው ያልፋል ።

እጅግ ኋላ ቀር በሆኑት አገሮች ለሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ ባለመኖሩ ድንቁርና ሥር የሰደደ በመሆኑ የጤና አገልግሎት እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ፡ የያንዳንዱ ቤተሰብ የገቢ ምንጭ የነጠፈ በመሆኑ ፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ ማሳደግ የሚችለውን ብቻ የመውለድ እቅድ ባለመኖሩ የሚወለዱት ልጆች ከሕፃንነት ቢያልፉ በወጣትነታቸው ፡ ከወጣትነት ቢያልፉ በጐልማሳነታቸው ይቀሰፋሉ ።

ይህን በሚመለከት ጉዳይ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ከፍተኛ ጥናት አካሂዷል ። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው እጅግ ኋላ ቀር በሆኑ አገሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ ፩ ሽህ ሕፃናት ቢወለዱ ከነዚህ ውስጥ በልዩ ልዩ ደዌና ተውሳክ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ፪፻ ሕፃናት ይሞታሉ ። በዚህ አንፃር በሠለጠኑት አገሮች ፩ሽህ ሕፃናት ቢወለዱ በልዩ ልዩ ምክንያት ሦስት ዓመት ሳይሞላቸው ሊሞቱ የሚችሉ ፲፱ ብቻ ናቸው ኋላ ቀር በሆኑት አገሮች አንድ ዶክተር ለ፲፯ሽህ ሰዎች ሲመደብ በሠለጠኑት አገሮች አንድ ዶክተር ለ፭፻፳ ሰዎች ብቻ ይመደባል ። ኋላ ቀር በሆኑት አገሮች የያን

ወደ ፲፱ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# በትምህርት አሳቦ ልመና

“ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ሄዳችሁ አስተምሩ” ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ተግባራዊ ለማድረግ አሥራ ሁለት ሐዋርያት እጣ ተጣጥለው ለዓለም ሁሉ የወንጌልን ቃል ለማዳረስ ብዙ ጥረት አድርገዋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን “በከንቱ ዘነሣእክሙ ሀቡ በከንቱ” ያለዋጋ የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ የተባለውንም ቃል በመጠበቅ በደረሱበት ሁሉ በነፃ አስተማሩ እንጂ ከማንም ስለድካማቸው ዋጋ አልተቀበሉም ። ይልቁንም ውድ ሕይወታቸውን ስለክርስቶስና ስለወንጌል መሥዋዕት አድርገው በመክፈላቸው ታሪካቸው የገነነ ሆኖ በገድላቸው ሲነበብ ይኖራል ።

“ ከመምህሩ ደቀመዛሙሩ” እንደሚባለው ከነሱ ጋር የነበሩት ሰብአ አርድእትና ከነሱም በኋላ የተነሱት ጻድቃን ሰማዕታት ቀጥሎም የተተኩት ቅዱሳን አባቶች የሐዋርያትን አሠረፍኖት በመከተል ወንጌልን እያስተማሩ ሕይወታቸውን ከማሳለፍ በቀር በገንዘብ ተደልለው ከወንጌል ትምህርት ወደኋላ ያሉበት ጊዜ እንደሌለ ከታሪክ እንማራለን እንዲያውም በጾምና በጸሎት እየተወሰኑ እራሳቸውን ለሕገ ወንጌል ከማስገዛት በቀር ለራሳቸው ጥቅም የሚሆነውን ነገር በመሻት በወንጌል ስም ነግደው የሚያውቁ አልነበሩም ። በርግጥ አንዳንድ ጊዜ ከምእመናን ላይ ገንዘብ እየሰበሰቡ በጎ አድራጎት ሲፈጽሙ የነበሩ አባቶች ሊኖሩ ይችላሉ ።

ይኸውም ፩ኛ ርዳታ ጠይቀው ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ፪ኛ በገዳም ዘግተው የሚኖሩትንና በበረሃም በዱር በገደሉ ወድቀው በጸሎትና በምናኔ በምህላም ፈጣሪያቸውን ተማጽነው በብቃት ደረጃ ያሉትን ፣ ባሕታውያን ለመርዳት ፍላጎት እያላቸው ጊዜ ለማያዳርሳቸው ምእመናን ተላላኪ ሆነው ከምእመናን ገንዘብ ተቀብለው በሚገባ ለማድረስ ፫ኛ ረዳት አጥተው የሚልሱትና የሚቀምሱት የሌላቸውን ችግረኞች ለመርዳት ሲሉ ዓላማውን ገልጠው ምእመናኑን በማሳመን የተገኘውን ያህል ርዳታ ከተቀበሉ በኋላ ከተሰጡት ርዳታ ምንም ባያጓድሉ እንደ አስፈላጊነቱ በመፈጸም ተልእኳቸውን ያደርሱ እንደነበር የታወቀ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ መልካም አርአያ ተዘንግቶ አንዳንድ በስም ባሕታውያን የሆኑ የወንጌል ትምህርት መነገጃና ገንዘብ ማግኛ እያደረጉት ይገኛሉ። ለምሳሌ በከተማውና በየገጠሩ እየተዘዋወሩ ወንጌልን እናስተምራለን በማለት በየቤተ ክርስቲያኑ የሚያካሂዱት የገንዘብ ስብሰባ ፕሮግራም ሕጋዊ ካለመሆኑ የተነሣ ገንዘብ ላላወቀበት ሰይጣን ነውና ደህናዎቹን እንኳን እስከማሳሳት እየደረሰ ግላዊ ጥቅም ይለምዱና ውሸት እየፈጠሩ ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ሙከራ ያደርጋሉ ።

ለምሳሌ በዚህ ሀገር እንደዚህ ያለ ቤተክርስቲያን ተቃጥሎ የሚያሠራው አጥቷል እንደዚህም ባለ ሀገር ጥንታዊ ገዳም በገንዘብ እጦት ተዘግቷል ። በእንደዚህ ያለ ሀገር ደግሞ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ የሚያሳድሰው በማጣቱ አስጀምሬ ሥራው እየተጠናቀቀ ነውና ማስፈጸሚያ ገንዘብ ጣል ጣል አድርጉ በማለት ልመና ይጀምራሉ በጎ አድራጎት ልምዳቸው የሆነው የኢትዮጵያ ምእመናንም አገሩ የትነው? ነገሩ ምንያህል እውነት ነው? ማስረጃ የትአለ? ብለው ሳይጠይቁ ከነአባ አፍ ውሸት አይወጣም በማለት ብቻ ያላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

፪ኛ/ በእንደዚህ ያለ ቦታ (ገዳም ያሉ) ባሕታውያን መነኮሳት የሚረዳቸው ስላጡ ሊበተኑ ነውና ማኅበሩ እንዳይፈርስ ለምኜ እንድረዳቸው እግዚአብሔር አዞኛልና እናንተም በረከት እንድታገኙ አስተዋጽኦ አድርጉ በማለት ስፋት ለምእመናን ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝን ያለ ጥያቄ ያቀርባሉ ። በዚህ ጥያቄ መሠረት ምእመናኑ ሳይጠራጠሩ ገንዘባቸውን ይሰጣሉ።እነሱ ግን ገንዘቡን ተቀብለው ለተባለው ቦታ ማድረስ ሲገባቸው ገንዘቡ በዚያው የውኃ ሽታ ሆኖ ይቀራል ። ጧት የተሰጡት ገንዘብ ከሰዓት በኋላ ባልሆነ መንገድ ሲባክን ማየት ለምእመናን ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝናቸው አይኖርም ። ታዲያ በዚህ ጊዜ የሚያደናቅፉት ግለሰቦቹን ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ነው ከዚህም ጋር ወንጌልን ያለደመወዝ በነፃ ሲያስተምሩ የኖሩት ቅዱሳን አባቶችም በነዚህ ዓላማ የለሾች ምክንያት ሊሰደቡና ሊጠሉ ይችላሉ ። ከኑግ ጋር ያለህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ” እንደተባለው ነውና ።

በአሁኑ ጊዜ የከተማው ሕዝብ እየነቃ ስለሄደና ምንጩም እየደረቀ በመምጣቱ ገንዘብ የማግኛቸው ዘዴም በመንጠፉ ከተማውን እየለቀቁ በክፍለ ሀገር በአውራጃና በወረዳ በገጠርም ጭምር ተበትነው ከምናኔ ዓለም የመጡና እውነተኞች መምህራን በመምሰል የስም ባሕታውያን አሁንም ለወንጌል ሳይሆን ለጥቅም እንደተሰለፉ ናቸው ።

በመሠረቱ የገንዘብ ጥያቄ የሚያደርጉት ወንጌልን ካስተማሩና በቃል ካነበቡ በኋላ በመሆኑ ሰሚዎች ምእመናን ወንጌላውያን ይዋሻሉ ብለው አይገምቱም ከዚህም የተነሣ ያቅማቸውን ያህል ከመስጠት ወደኋላ አይሉም ቆዳ ለብሰው ሰንሰለት ታጥቀው የሚያስተምሩ ባሕታውያን እንዴት ሊጠረጠሩ ይችላሉ? ማስተዋል የሚገባው ግን ወታደር ሳይሆኑ የወታደር ልብስ ለብሰው በወታደር ስም ለማታለል የሚሞክሩ እንዳሉ ሁሉ የብሕትውና ልብስ ለብሰው የምንኩስና ቆብ ደፍተው ሳይመነኩሱ መነኩሴ የሚመስሉ ሳይመንኑ ቀን ቀን ብቻ ባሕታውያን የሚሆኑ ለጥቅም የተገዙ የስም ባሕታውያን እንደማይታጡ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ምናልባት የወንጌል ማስተማር ፍላጎት እያላቸው መተዳደርያ በማጣት ከሆነ በወንጌል ስም የሚለምኑት ያልሆነውን ሆነ በማለት ሳይሆን ትክክለኛውን ዓላማ በመከተል ችግራቸውን ለምእ

ወደ ገፅ ፳፩ ዞሯል



## አለቃ ሺዋጋህ...

ከገፅ ፲፭ የዞረ

ሚያምኑት ሰዎች ምሳሌ ሁን ሲል ለጢሞቲዎስ የለገሠለትን መንፈሳዊ የምክር ቃል አለቃ ሺዋጋህ በሥራ በመተርጎም በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ከኑሮ ጓደኛቸው ጋር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ከሚገኘው መካነ ኢየሱስ ከተባለው ታላቅ ደብር ከሚገኙት መምህር ኃ/ሚካኤል የምንኩስና ማዕረግ ተቀብለዋል።በሌላ በኩል አለቃ ሺዋጋህ እንደበታቸው ፣ ከጸሎትና ፈጣሪያቸውን ከማመስገን ሰውነታቸው ከንጽሕና እጃቸው ከምጽዋት ያልተለየ በጠቅላላው ሰውነታቸውን የእግዚአብሔር ማደሪያ ያደረጉ መንፈሳዊ አባት ነበሩ ።

አለቃ ሺዋጋህ አሰማኸኝ ምንም እንኳን ሰውነታቸውን ለእግዚአብሔር ማደሪያ ያደረጉ መንፈሳዊ አባት ቢሆኑም መሬት ነህና ወደ መሬት ተመለስ የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ በመፈጸም በተወለዱ በ፹፯ ዓመታቸው ጥቅምት ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

## የኀዘን መዝሙር

አለቃ ግብርህን ለልጅህ አውርሰው ፣
እውቀትህንማ መቃብር ወረሰው ።
ወረቡን በሥረይ ስታንጐራጉረው ፣
ሰውስ ይቅርና ይደሰታል እውሬው ።
ወይ አገሬ ቅስናጥ የሊቃውንት ቦታ ፣
ሕንፃው ብቻ ቀረ የሌለው ውለታ ።
መቋሚያውን ፣ ስጡኝ ላልቅስበት ዛሬ፣
ጽናጽሉን ስጡኝ ላልቅስበት ዛሬ፣
ከእኛ ከተለየ አባታለም ክብሬ ።
ሁሉም ቢመራመር በወቅትም ቢለካ
ፈጽሞ አይገኝም አንተን የሚተካ ።
መለየት የሚሉት የልጆች ባላንጣ፣
አባት አለም ቀረ ከቤቱ እንደወጣ ።
ችግሬን ልንገርህ ተነስ በሥላሴ ፣
አንተ አልነበርክም ወይ ካባዬ ቀሚሴ።
በአንድ ላይ ስንኖር ለረዥም ወራት ፣
ከፍቅር በስተቀር የለም ብስጭት ።
ተነስ አባታለም እንየው ፊትህን ፣
በፍቅር ሰንሰለት ታስረናል ሁላችን ።
ማኅሌት ገብቼ ቁሜ ስሰማህ ፣
ይመስለኝ ነበረ ሞት የማይነካህ ።
ቅስናጥ እስጢፋኖስ የበቀለው ዛፍ ፣
ፍሬውን አርግፏል አንድም ሳያተርፍ ።
ቁሜ ስጠይቀው ቀለሙን በተራ ፣
ይመስለኝ ነበረ የአባት ባልንጀራ ።
ከመቃብር ገብቶ ሲዘምር ዝማሬ ፣
ያነጓድጓድ ድምጹ አልተሰማም ዛሬ ።.
አለቃ ሺዋጋህ በላይኛው ቦታ ፣
ለዘመዶቻቸው ያቅርቡ ሰላምታ ።
ሺዋጋህ ነበረ የጥበብ ምንጫችን ፣
የምናረካበት መላ ህይወታችን ።
ፋርጣ ደብረታቦር እራበይ አገሬ ፣
ሊቃውንቶቻችን ተጨረሱ ዛሬ ።
የእስጢፋኖስ ሕንፃ ወርቅ የፈሰሰበት ፣
ሊቃውንቱ አለቁ የሚዘምሩበት

የዜናው አቅራቢ. መ/ ወርቁ ውብሸት

## እርጅና

ከገፅ ፲፯ የዞረ

ዳንዱ ሰው ማዕከላዊ ዕድሜ 45 ዓመት ሲሆን በሠለጠኑት አገሮች የያንዳንዱ ሰው ማዕከላዊ ዕድሜ ፸ ዓመት ነው እንዲያውም በሚቀጥሉት ፳ ዓመታት ማለት እንደ እ.አ. በ፪ሺህ ዓ.ም. በሠለጠኑት አገሮች የያንዳንዱ ሰው ዕድሜ ወደ ፩፻፲ ዓመት ከፍ እንደሚል በጥናት ተደርሶበታል ።

በበለፀጉት አገሮች በሽታ ፣ ድንቁርና ፣ ረሃብና እርዛት እየተወገዱ በመሄዳቸው የአንድ ሰው ዕድሜ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ሊራዘም ችሏል ይህ ሁኔታ በአንፃሩ ቀድሞ ያልነበሩ ችግሮችን አስከትሏል ።

የሠለጠነው ዓለም እንደሦስተኛው ዓለም ሰፊ ቤተሰብ ስለሌለውና ሁሉም እራሱን ችሎ ስለሚኖር አንድ ሰው ዕድሜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ብቸኝነቱም በዚያው ልክ እየተባባሰ ይሄዳል። የቤተሰብ ፍቅር የመነመነው ። በሀገራችን እንደሚታዩው ሽማግሎች በልጅ ልጅ ተከበው ተረት የሚያወሩት ታሪክ የሚተርኩበት አጋጣሚ ጊዜ የላቸውም አረጋውያኑ በሚያገኙት የጡረታ አበል ገበያ ሄደው አስቤዛ ገዝተው ራሳቸው አብስለው መመገብ አለባቸው ። በሠለጠነው የቤት ሠራተኛ የሚባል ስለሌለ በደከመ ሰውነት ምግብ ማዘጋጀት ቤት ማጽዳት ልብስ ማጠብና የመሳሰሉት ነገሮች እንደከባድ ሸክም የሚቆጠሩ ናቸው ።

ሌላው ከባድ ችግር ብቸኝነት ነው ። እግዚአብሔር ያደላቸው ባልና ሚስት በሽምግልና ዘመናቸው አብረው የሚኖሩ ከሆኑ ሁለቱ እየተረዳዱና እየተወያዩ ኑሮአቸውን ይገፉታል ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በአውሮፓ ከተማዎች በብዛት በዕድሜ ገፍተው የሚታዩት በ፪ኛው ዓለም ጦርነት ባሎቻቸውን ያጡ መበለታት ናቸው ። እያንዳንዱ ሰው ጊዜ ስለሌለውና ሁሉም የዕለት ኑሮውን ለሟሟላት ስለሚባክን መበለታቱን ዘወር ብሎ የሚያያቸው የለም ። ልጆች እንኳ ቢኖሩአቸው ሊጠይቋቸው የሚችሉት በዓመት አንድ ጊዜ ለልደት በዓል ብቻ ነው ። በዚህ ምክንያት ድመትና ውሻ እያሳደጉ ይሰሙአቸው ይመስል የሚያስቡትን ሁሉ ለነርሱ ሲያወሩ ይውላሉ ።

አረጋውያን እንደማንኛውም ሰው እንክብካቤና አክብሮት ያስፈልጋቸዋል። ሽማግሌ ይመክራል ፣ ያስተምራል ያስታርቃል ፣ ጫወታውም ያዝናናል በዚሁ መልክ አረጋውያን አጸፋውን ማግኘት አለባቸው ።

የአረጋውያንን ፍላጎት ለማርካት ብዙ አገሮች በብዙ መንገድ በመጣር ላይ ናቸው ። በእርጅና ምክንያት የሚፈጠሩትን በሽታዎች ለመከላከል ልዩ ዶክተሮች እየሠለጠኑ ነው ። ለሽማግሌዎች መጠሪያ ከፍተኛ በጀት ተመድቦ ታላላቅ ሆስቴሎች ተሠርተዋል ። በአ



www.ethiopianorthodox.org

ንድ አንድ አገሮች ጡረታ ለወጡ ሰዎች ልዩ ትምህርት ቤት ተከፍቶላቸው በወጣትነት ዘመናቸው ሳያገኙ የቀሩትን ትምህርት በማግኘት ራሳቸውን እንዲያስደስቱ ይደረጋል ። የፈረንሳይ መንግሥት የአረጋውያንን ጉዳይ የሚመለከት ራሱን የቻለ ጽ/ቤት ከፍቶአል ። ይህ ጽ/ቤት አረጋውያንን በጉልበት የሚረዱ ሰዎች በመቅጠር ፣ የጤና ባለሙያዎችን በመመደብ ልዩ ልዩ የመዝናኛ ፕሮግሞችን በማዘጋጀት ሽማግሎች ያላቸውን ዘመን ሳያዝኑናሳይተክዙ እንዲያሳልፉ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል ።

ይህን በሚመለከት ሁኔታ ወደ ሀገራችን መለስ ብለን ስንመለከት ከልጆች ይልቅለሽማግሎችልዩከበሬታናእንክብካቤ ሲደረግ ቆይቷል።ይህም ሊሆን የቻለበት ምን አልባት በሀገራችን የሽማግሎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ስለሆነና እንደብርቅ ስለሚታዩ ሊሆን ይችላል ሆኖም ዓላማው ጥሩ ስለሆነ በዚሁ ሊገፉበት ያስፈልጋል ።

በባሕላችንና በሃይማኖታችን አረጋውያንን ማክበር ጤና ይሰጣል ፣ የሰላምና የተባረከ ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋል ። ሽማግሌ የመረቀው ሰው ሕይወቱ የተሟላ ነው ። በዚሁ አንፃር ደግሞ ሽማግሌ የረገመው ሰው ኑሮው እስከፊና መራራ ነው ። ከዚህ ልምድ የተነሣ አበው ሽማግሌ አይርገምህ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚለውን የንግግር ዘይቤ አዘውትረው ሲናገሩ ይሰማሉ ።

ማንኛውም ኅብረተሰብ አረጋውያንን የመንከባከብ የውዴታ ግዴታ አለበት ። ምክንያቱም የአንድ ኅብረተሰብ ሕልውና የተመሠረተው በነርሱ ደምና ላብ ስለሆነ ነው ። ይህን በሚመለከት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፰፻፳፩ ከፊደል ሀ እስከ ሰ ድረስ ተወላጆች ወላጆችን የመጦር ግዴታ እንዳለባቸው በዝርዝር ይደነግጋል ።

በሰሜን ኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገሮች አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢቀርና ጧሪ ቀባሪ ባይኖረው ኅብረተሰቡ የመጦር ግዴታ አለበት ይህም እልፍ ይባላል ። እልፍ ማለት አንድ ሰው በቁሙ ያፈራው ሀብት ንብረት ወይም አቅፎ ደግፎ የሚይዘው ዘመድ አዝማድ ሳይኖረው በእርጅና ምክንያት ሠርቶ መብላት ሲሳነው በአካባቢው ከሚገኘው ከአንዱ ሰው ቤት ደጃፍ ሂዶ ይቀመጣል ። የቤቱ ባለቤት ይህን ሰው ተቀብሎ የሚበላውን ማብላተ የሚጠጣውን ማጠጣት ያለበት መሆኑን የኅብረተሰቡ ባሕል ያስገድደዋል ። በዚህ ሁኔታ የቤቱ ባለቤት ሽማግሌውን የሚበቃውን ቀን ያህል ያስተናግድና ሲያበቃ ከሚቀጥለው ጉረቤት ደጃፍ ወስዶ ያስቀምጠዋል ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌውን ከማስተናገድ በስተቀር ለምን አመጣህብኝ ብሎ መቆጣት ወይም መጣላት የለበትም የሚችለውን ቀን ያህል አስተ



የኤድሜ ፀጋ ከአገኙት አዛውንት አንዱ

ናግዶ ሲበቃው ወደሌላው ቤት ያስተላልፋል ።

በዚህ ሁኔታ ለሽማግሌው የኅብረተሰቡ ቤት ቤቱ ስለሆነ ምንም ዓይነት ችግር ሳይደርስበት የተወሰነለትን ዕድሜ ይፈጃል ። በሞተም ጊዜ የአካባቢው ኅብረተሰብ በወጉና በሥርዓቱ ተላቅሶ ይቀብረዋል ። እንደ እምነቱም ፍታቱን ያስፈታለታል ።

አረጋውያንን በመንከባከብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋኦ ስታበረክት ቆይቷለች አሁንም እየበረከተች ነው ። በተለይ ሥርዓተ ገዳም በዚህ በኩል ጠበቅ ያለ ሕግ አለው ። እንደሚታወቀው የገዳም ሥርዓት የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አሉት ከሥራው ክፍል አንዱ የደከሙ ሽማግሎችን መርዳት ነው ።

ልጅነት ያለው መነኩሴ እንደአባቱ ተንከባክቦ የሚረዳው አንድ አረጋዊ ይሰጠዋል ። መነኩሴው በአላፊነት እንዲረዳው የተሰጠው አረጋዊ እስከ አረፈበት ጊዜ ድረስ ልብሱን አጥቦ ፣ ሠርክ ሕብስቱን በተወሰነው ሰዓት አቅርቦ ሌላም የሚያስፈልገውን ሁሉ እየጠየቀ በማቅረብ መርዳት አለበት ። ይህም ለምንኩስና ሕይወት ከሚሰጠው አንዱ ትልቅ ፈተና ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኅዙናን ስለሆነች ተስፋ ቅቡፃን የሆኑ ሰዎች ሁሉ እርሷን መጠጊያ አድርገው ኑረዋል ። ቤተ ክርስቲያንም የታመመውን በመፈወስ የታረዘውን በማልበስ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያን በመንከባከብ ከፍተኛ ማኅበራዊ አገልግሎት ስታበረክት ቆይታለች ።

ይህን የመሳሰለው በጎ አድራጎት ሲካሄድ የቆየው ምዕመናን በግላቸው በሚያደርጉት እርዳታ ነው ። አሁን ጊዜው ከግላዊነት ወደ ማኅበራዊነት አገልግሎት የተለወጠበት ነው ። ምዕመናን 'ሚያደርጉት አስተዋጽኦ በአንድ ላይ እየተጠራቀመ ችግረኞች መረዳት አለባቸው ።

ምንም እንኳን የመንግሥት ሥራ ሲሠሩ ለኖሩ ሰዎች የጡረታ መብት ቢፈቀድ በልዩ ልዩ ሙያ ተሰማርተው ሀገራቸውን ሲያገለግሉ የኖሩ አዛውንቶች በሽምግልና ዘመናቸው መጠጊያ አጥተው በቤተክርስቲያን ዙሪያ ወድቀው ምጽዋት ሲለምኑ የሚታዩ ብዙዎች ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን በማስተባበር መካነ አበው እያዘጋጀች ዘመድ አዝማድ የሌላቸውን አረጋውያን ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ የመጦር ኃላፊነት አለባት ። ይህም እምነትንና ምግባርን ስለሚያስተባብር ዓላማዋን እንደ ፈጸመች ያስቆጥራታል ።

በመሠረቱ እርጅና በሽታ አይደለም ። እርጅና ፀጋ ነው ። ሽማግሌ ያለበት ቤተሰብ የታፈረና የተከበረ ነው ። ሽግሚሌ·

ወደ ገፅ ፲፯ ዞሯል



# በትምህርት አሳቦ.....

ከገጽ ፲፭ የዞረ

መናኑ ቢያቀርቡ የሚያበቃቸውን ያህል ሊሰጡዋቸው ስለሚችሉ ደመወዝ እስከሌላቸው ድረስ በዚህ በኩል ሊነቀፉ የሚችሉ አይመስለኝም"ኢትቀውም ነፍስ ዘእንበለ ሥጋ ነፍስ ያለ ሥጋ ቆማ መንቀሳቀስ እንደማትችል የታወቀ ከመሆኑም በላይ ለሠራተኛ ደሞ ዋጋው ይገባዋል"ተብሎ ተጽፏልና።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ፩ኛ ቆሮንቶስ ፱፡ ፲፫ በጻፈው መልእክቱ "በመቅደስ የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሆነውን ነገር እንዲመገቡ በመሠዊያውም የሚፀኑ ከመሠዊያው እንዲካፈሉ አታውቁምን? " ካለ በኋላ እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል" ሲል ከማስረዳቱም በላይ ቀደም ሲል በቁጥር ፯ ደግሞ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ፣ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማነው? ይልና የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሠረው ተብሎ የተጻፈው ስለወንጌል መምህራን የተነገረ መሆኑን በሰፊው አብራርቷል ። ስለዚህ እውነተኞች ሐዋርያት ለእለት ምግባቸው ለዓመት ልብሳቸው የሚያስፈልጋቸውን በግልጥ ከምእመናን ይጠይቃሉ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ይቀበላሉ እንጂ በተዘዋዋሪ መንገድ በወንጌል ስም ሊነግዱና ሊያተርፉ አይፈቅዱም። ስለዚህ ስለጸድቅ ሳይሆን ገንዘብ ለመለመን አመች ይሆንላቸው ዘንድ ወንጌልን እያስተማሩ ከወንጌል ቃል,ጋር እንዳዳንድ ሁኔታዎችን አስመስለው በመናገር የልመና መረባቸውን የሚዘረጉ ቢኖሩ ምእመናንን ፡ ከማሳዘን ይጠንቀቁ ቤተ ክርስቲያንም ሁኔታውን እየመረመረች ወንጌልን የማስተማር ፍላጎትና ችሎታ ያላቸውን በሥራ ብታሠማራቸው ሁኔታው መልክ ይይዛልና ቢታሰብበት መልካም ነው ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

# ትምህርት ግዕዝ

# የግዕዝ ትምህርት

ትምህርት ፲፫ ሥርዓተ ገቢር ወተገብሮ

ገቢር ፡ ማለት የሚሻገር ግሥ ማለት ነው ።

ተገብሮም ፡ ማለት የማይሻገር ግሥ ማለት ነው ።

በልሳን ግእዝ ግሡ ተሻጋሪ ሲሆን የግሡ ተጠሪ

ሀ- መድረሻ ፊደሉ ሣልስ ከሆነ ወደ ሐምስ

ለ- መድረሻ ፊደሉ ሳድስ ከሆነ ወደ ግዕዝ ይለወጣል ።

ለምሳሌ፦ የሚከተሉትን ቃላት ጸፍና ዐረፍተነገር እየሠራን እንረዳለን ።

| ቃላት (ግዕዝ) | | ቃላት (ሣልስ) | |
|---|---|---|---|
| ፈያታይ | ወንበዴ | ጠሊ | ፍየል |
| ፈያት | ወንበዴዎች | ሰያጢ | ሻጭ |
| ፀር | ጠላት | ነጋዲ | ነጋዴ |
| አፅራር | ጠላቶች | ኢትዮጵያዊ | የኢትዮጵያ ዜጋ |
| | | አግዓዚ | ነፃ አውጭ |
| ግብር | ሥራ | ነባሪ | ቤተ ሰብ |
| ቀቲል | መግደል | ቀናኢ | ቀናተኛ |
| ረኪብ | ማግኘት | ብእሲ | ሰው (ወንድ) |

## ዐረፍተ ነገር

| | |
|---|---|
| ገቢር መስተሳልም ቀተለ ፈያታየ፡፡ | ፀጥታ አስከባሪው ወንበዴውን ገደለ |
| ተገብሮ ፈያታይ ተቀትለ በእደ መስተሳልማን | ወንበዴው በፀጥታ አስከባሪዎች እጅ ተገደለ |
| ገቢር መስተሳልማን ቀተሉ ፈያተ | ፀጥታ አስከባሪዎች ወንበዴዎችን ገደሉ |
| ተገብሮ ፈያት ተቀትሉ በእደ መስተሳልማን | ወንበዴዎች በፀጥታ አስከባሪዎች ተገደሉ |
| ገቢር ትጉሕብእሲ ረከበ ግብረ | ትጉህ ሰው ሥራን አገኘ |
| ተገብሮ ኢተረከበ ግብር ለሐካይብእሲ | ለሰነፍ ሰው ሥራ አልተገኘም |
| ገቢር አፈቅር አነ ኢትዮጵያዌ | እኔ ኢትዮጵያዊውን እወዳለሁ |
| ተገብሮ ኢትዮጵያዊ ኮነ አግአዜ | ኢትዮጵያዊ ነፃ አውጭን ሆነ |
| ገቢር ሐራሲ ያፈቅር ነጋዴ | ገበሬ ነጋዴን ይወዳል |
| ወነጋዲ ያፈቅር ሐራሴ | ነጋዴም ገበሬን ይወዳል ። |
| ገቢር ፡ ነጋዲ አቅረበ በግዓ ለሕዝብ | ነጋዴው ለሕዝብ በግን አቀረበ |

መዘክር ራብዕ ፡ ሐምስና ሳብዕ በገቢር በተገብሮ ሳይለወጡ ሊነገሩ ይችላሉ

ለምሳሌ ፦

| | |
|---|---|
| አስተርአየ ደመና ላዕለ ሰማይ | ደመና በሰማይ ታየ |
| ርኢኩ ደመና ላዕለ ሰማይ | በሰማይ ደመናን አየሁ |
| አስምኡ ሕዝብ ይባቤ | ሕዝቡ እልልታን አሰሙ |
| ተሰምአ ይባቤ እምሕዝብ | ከሕዝቡ እልልታ ተሰማ |



www.ethiopianorthodox.org

# የጤና አምድ

ካለፈው የቀጠለ

## ተላላፊ በሽታ

ተላላፊ በሽታ አዘውትሮ የሚያጠቃው እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች የሆኑትን ሕፃናት ሲሆን በዚህም ምክንያት ሕይወታቸውን እስከማጣት የሚደርሱ ሕፃናት ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ ነው ። በአገራችን ውስጥ በዚሁ እድሜ ክልል ውስጥ ከሆኑት ፩ ሺህ ሕፃናት በዓመት ሲሞቱ በሰለጠኑ ሀገሮች ግን ፩ ብቻ ይሞታል ። እንግዲህ ይህን ሁኔታ ለመቋቋም የእያንዳንዱ ቤተሰብ ጥረት ያስፈልጋል ።

ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ከሚያስችሉት ዘዴዎች ውስጥ ሕፃናትን የግልና የአካባቢን ጽዳት መጠበቅ የተጣራ ውኃ መጠጣትና በንጽሕና የተጠበቀና በሚገባ የበሰለ ምግብ መመገብ ዋናዎቹ ናቸው ።

ሕፃናት በበሽታ ከተለከፉ በኋላ ለማዳን ከመሞከር ይልቅ በሽታ እንዳይዛቸው አስቀድሞ መጠንቀቅ ዓይነተኛ ዘዴ ነው ። ለዚህም ከሚረዱት ውስጥ አንዱ ክትባት መሆኑ እላይ ተጠቅሷል ። በክትባት ለመከላከል የሚችሉት ልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች የሚከተሉት ናቸው ።

1/ ኩፍኝ /እንኪሊስ/
2/ ትክትክ/ ቋቋት/
3/ ዘጊ እንዳ /ዲፒቴሪያ/
4/ የሳንባ ነቀርሳ
5/ መንጋጋ ቆልፍ/ቴታነስ/
6/ የሽባ በሽታ/ፓሊዮ/
7/ ፈንጣጣ/ወተቴ/

1ኛ/ የኩፍኝ በሽታና መከላከያው የኩፍኝ በሽታ በሀገራችን ውስጥ በየዓመቱ የብዙ ሕጻናትን ሕይወት የሚያጠፋ በሽታ ነው ። ሕመሙ የሚጠነክረውና እየተባባሰ የሚሄደው ጠቅላላ ጤንነታቸው ባልተጠበቀ ፣ የምግብ እጥረትና የተቅማጥ በሽታ ባለባቸውና ጡት በማይጠቡ ሕፃናት ላይ ነው ። እስከሞት የሚያደርሰውም ራሱ ኩፍኝ ሳይሆን ሌሎች አደገኛ ሕመሞችን የሳንባ ፣የልብና የኩላሊት በሽታዎችን ሊያስከትል ስለሚችል ነው ።

ኩፍኝን የሚያመጣው በዓይን የማይታይ ረቂቅ ሕዋስ ሲሆን የሚተላለፈውም በሳል ፣በትንፋሽ ፣ ሕመሙ ከያዘው ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግና ሕመምተኛው በተጠቀመባቸው ዕቃዎችና ልብሶች በመጠቀም ነው ። በሀገራችን ውስጥ በብዙ ወላጆች እንደሚታመነው የኩፍኝ በሽታ በሰው ዓይንና በጥላ ሊመጣ አለመቻሉን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ።

ኩፍኝ ሲጀምር እንደጉንፋን ሆኖ የጉሮሮ ሕመምና መቅላት ፣ ትኩሳት ፣ የአፍንጫ መዝረክረክና የምግብ ፍላጐትን መቀነስ ያስከትላል ። እነዚህ ምልክቶች መታየት በጀመሩ በአራተኛው ቀን አካባቢ ሽፍታው ይወጣል ። በመጀመሪያ በግንባርና በፊት ላይ ከዚያም በመላው የሰውነት ክፍል መታየት ይጀምራል ።

ኩፍኝ የያዘው ሕፃን ገላውን የታጠበ እንደሆነ ወይም መርፌ የተወጋ እንደሆነ በሽታው ወደ ሆዱ ይገባል የሚለው ጥንታዊና ባህላዊ እምነት ትክክል አይደለም ። በተጨማሪም ንፍሮና ቆሎ ወደ ውጭ በመርጨት የኩፍኝን በሽታ ለመከላከልም ሆነ ለማስታገስ አይቻልም ።

ኩፍኝን ለመከላከል የሚቻለው ሕፃናትን በማስከተብ ብቻ ነው ። ሕፃናት ተወልደው ስድስት ወር እኪሆናቸው ድረስ ለኩፍኝ በሽታ ከእናታቸው የወረሱት መከላከያ ኃይል ይኖራቸዋል ።ከዚህ በኋላ ግን የመከላከያው ኃይል እየደከመ ስለሚሄድ በሽታው በቀላሉ ሊይዛቸው ስለሚችል በዘጠኝ ወራቸው የኩፍኝ ክትባት ማስከተብ ያስፈልጋል የኩፍኝ ክትባት ለብዙ ዓመታት ከበሽታው ሊጠበቅ ስለሚችል እንደሌሎቹ ክትባቶች መደጋገም አያስፈልግምየኩፍኝ በሽታ ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች በሆኑ ሕፃናት ላይ የሞት አደጋ ሊያደርስባቸው ስለሚችል ክትባቱን በተጠቀሰው ጊዜ እንዲወስዱና ከመከተባቸው በፊት ኩፍኝ ከያዛቸው ልጆች ጋር እንዳይገናኙ መከልከል ነው።

የኩፍኝ በሽታ /ወረርሽኝ/ በሰፈሩ ከገባ በኋላ ክትባት ቢሰጥ በሽታው በሕጻኑ ላይ እንዳይበረታበትና ወደ ሌላ ቀበሌ እንዳይዘምት ከመርዳቱ በስተቀር ሕጻኑን ከበሽታው ለመጠበቅ ዋስትና ስለሌለው በተጠቀሰው ጊዜ ማስከተብ ጠቃሚ ነው ።

፪ኛ/ የትክትክ/ቋቋት/ በሽታ፡- ይህ በሽታ የሚያስቅቅ ተላላፊ በሽታ ነው ሕጻኑ በሳለ ቁጥር ትክትክ የሚል ድምጽ ያሰማል ትውከትም ያስከትላል ።ሕፃኑ በሚስልበት ጊዜ አየር ለመሳብ ያዳግተዋል ስለሚታፈንም ብዙ ይሰቃያል ለታመመው ሕፃን ይቅርና ለሚያየውና ለሚሰማው የሚያስቅቅ ነው የሚተላለፈውም በሳልና በትንፋሽ ሆኖ ከሞት ሊያደርስ የሚችል ነው ።

፫ኛ/ የመንጋጋ ቆልፍ በሽታ፡- ይህ በሽታ በማንኛውም እድሜ ሊይዝ ይችላል ሆኖም በብዛት የሚያጠቃው ሕፃናትን ነው በሽታው ሲይዝ መንጋጋን ይዘጋል ሰውነትን ያደርቃል ጡንቻዎችንም ያኮማትራል ። በሽታው የሚመጣው የዛገ ምስማር ፣ ሽቦ እሾህ ስንጥርና ማንኛውም ስለት ያለው ነገር ቆዳን ቆርጦ ወይም በስቶ በሚገባበት ጊዜ የበሽታው ረቂቅ ሕዋስ መርዝ በቁስሉ በኩል ገብቶ እንጉልን ስለሚወር ነው በተጨማሪም በተለይ በሀገራችን ውስጥ አዲስ በሚወለዱ ሕፃናት ላይ የሞት አደጋ ከሚያደርሱት ልዩ ልዩ በሽታዎች አንዱ ነው ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ሕፃናት በሚወለዱበት ጊዜ እምብርታቸው ባልፈላና ንጽሕናው በተጓደለ ምላጭ መቀስ ስለሚቆረጥና በተሳሳተልምድ እምብርታቸውላይ ቅቤጭቃ ናእበት የመሳሰሉትን በመቀባት ነው።የመንጋጋ ቆልፍ ሕዋስ የሚራባው በአፈር ውስጥ በተለይም እበት ፋንድያና ፍግ ባለበት አካባቢ በመሆኑ ይህ ድርጊት በጣም አደገኛ ነው ። ይህ በሽታ ተላላፊ አይደለም ይሁን እንጂ በክትባት ለመከላከል የሚቻል በመሆኑ ሊጠቀስ ተችሏል ክትባቱ የሚሰጠው ትክትክና ከዲፒቴሪያ ክትባት ጋር ተደባልቆ በአንድ ላይ ነው ። አዲስ የሚወለደውን ሕፃን ለመጠበቅ ነፍስ ጡር ሴቶች በተከታታይ በየወሩ ሁለት ጊዜ ቴታነስ ቶክሶይድ የተባለውን በመርፌ ቢወስዱ ጥሩ ነው ።

የዲፒቴሪያ የመንጋጋ ቆልፍና የትክትክ በሽታ ክትባት የሚጀመረው ሕፃኑ በተወለደ በሁለት ወር እድሜው ሲሆን ከዚህ በኋላ በየወሩ ሁለት ጊዜ በተከታታይ ይደጋገማል ይህ ካልሆነ ግን ግለትም እንዴ እስከትቦ ዝምቢሉ ክትባቱ ሊረዳ አይችልም ።

የሣንባ ነቀርሳን ለመከላከል የሚቻለው ሕጻናትን እንደተወለዱ በማስከተብ ነው ሐኪም ቤት ከተወለደ ከመውጣቱ በፊት እቤት ከተወለደም ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ክትባቱን እንዲወስድ ማድረግ እጅግ ጠቃሚነው።

የሽባ በሽታ የልጅነት ልምሻ በመባል ይታወቃል በሽታውን የሚያመጣው በሠገራ የሚገኝ ሕዋስ ሲሆን የእጅ የእግርና የደረት ጡንቻዎችንና እንቀሳቃሽ ሥሮችን እያደከመ እያደነዘዘና በድን እያደረገ የሚሄድ ኃይለኛ ተላላፊ በሽታ ነው።በዚህ በሽታ የተለከፉ ሕፃናት ግማሾቹ ሲሞቱ የተረፉት ደግሞ አካለ ስንኩል ሆነው ይቀራሉ ።

የበሽታው አጀማመር ከጉንፋን የተለየ አይደለም ። በመጀመሪያ የሚታዩት ምልክቶች ራስ ምታት ፣ ትኩሳት ፣ ድካም አልፎ አልፎም ተቅማጥና ትውከት ሲሆን በሽታው እየተባባሰ ከሄደ የወገብና የአንገት መጋጠሚያ ክፍል እየደረቀ ስለሚሄድ ሕመምተኛው ጎንበስና ቀና ማለት ያዳግተዋል ። በሽታው እጆቂዎችንም ሊይዝ ይችላል ። ይህንን በሽታ ለመከላከል ከክትባት ሌላ የአካባቢን ንጽሕና በሚገባ መጠበቅ ያስፈልጋል ።

እንግዲህ ሕፃናትን ከሞት ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን በሞላ ጎደል ተመልክተናል ። ጤንነታቸውንም ለመጠበቅ በአጠቃላይ ማስታወስ የሚገባን ክትባት በወቅቱ ማስከተብ ፣ ጡት ማጥባት ፣በጡጦ አለመጠቀም ፣ግግ አለማስወጣት ፣ እንጥል አለማስቆረጥ ፣የግልና የአካባቢ ንጽሕናን መጠበቅ ፣የተመጣጠነምግብ መመገብናከታመመው ወደወጌሻናባለውቃቢ ከመውሰድወደ ሕክምናባለሙያዎች መውሰድእንደሚገባ ነው ።

ከላይ እንደተመለከትነው ወደባለውቃቢ ሂዶ መለማመንም ሆነ በሽታውን ለማስታገስ ቆሎ መበተን ፣ አለሞቹ ለምለሞቹ እያሉ ማጉንበስ ሌላም ሌላ ዓይነት ድርጊት መፈጸም እንዳች መፍትሔ ካለማስገኘቱም ሌላ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሰይጣን የሚሰግዱ እናቶች ብዙዎች ናቸው ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ልክ እንዳልሆኑ ሲነገራቸው አቃቢ መልአክ የሚለውን ውቃቢ በሚለው ተርጉመው ሊሆን ይችላል ከእግዚአብሔር በታች እነርሱንም መለማመን አለብን ጠባቂዎች እንዲሆኑም ተሰጥተውናል የሚሉ አሉ ። ይሁን እንጂ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ኃይል ድል በመንሳት እንጂ በመለማመን አንዳችም ማትረፍ እንደማይቻል መረዳት ጠቃሚ ነው ።

ከመጽሐፍቅዱስውስጥሰዎች ከእግዚአብሔር ሌላ ማንም የሚያድናቸው ፣ በመከራቸው ጊዜም ሊረዳቸው የሚችል እንደሌለና ስግቸውንም እንኳ መጥራት እንደማይገባ በብዙ ክፍሎች እናገኛለን ። ለጊዜው ግን ሁለት ጥቅሶች ብቻ ብናይ በቂ ሊሆን ይችላል ።

ያልኋችሁን ነገር ሁሉ ጠብቁ የሌሎችንም አማልክት ስም አትጥሩ ከአፋችሁም አይሰማ ዘጸአት ፳፫ ቁ ፲፫

" እግዚአብሔርም ያዕቆብን አለው ተነስተህ ወደ ቤተልሄምውጣ በዚያም ኑር ከወንድምህ ከኤሳው ፊት በሸሽህ ጊዜ ለእግዚአብሔርም መሠውያውን አድርግ ። ያዕቆብም ለቤተ ሰቡና ከእርሱ ጋር ላሉት ሁሉ እንዲህ አለ እንግዶቹን ከመካከላችሁ አስወግዱ ንጹሐንም ሁኑ ልብሳችሁንም ለውጡ ተነስተንም ወደ ቤተልሔም እንውጣ በዚያም በመከራዬ ጊዜም ለሰማኝ በሄድሁበትም መንገድ ከእኔ ጋር ለነበረው ለእግዚአብሔ መሠውያን አደርጋለሁ"

።ተማሪ ነርስ የሺሐረግ ሥርጋዊ

## ደስታ

ይህ ያለንበት ምድራዊ ዓለም ሐዘንና ደስታ ፡ ሳቅና ዋይታ ፣ እየተፈራረቁበት የሚኖርና ሥጋዊ ደስታም ከመንፈሳዊ ደስታ ጋር ሁለቱ በእኩልነት የሚኖሩበት ቦታ መሆኑ አያከራክርም ።

ቢሆንም ሥጋዊ ደስታ በዓለም ውስጥ ጸንቶ የሚኖርና የሚታመን አቅዋም ያለው ሳይሆን ኃላፊና ጊዜያዊ ነው ።

ነቢዩ ኢሳይያስም ስለጊዜያዊ ደስታ ሲገልጽ እንዲህ ይላል "እነሆ ሐሴትና ደስታ ፣ በሬውንና በጉንም ማረድ ሥጋንም መብላት የወይን ጠጅንም መጠጣት ሆኖአል እናንተ ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ (እንደሰት) ብላችኋል ይህ ነገር በሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ተሰማ እስክትሞቱም ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሠረይላችሁም" ብሏል ኢሳ ፳፪፡፲፫ ።

ነቢዩ እንደ ገለጸው ሥጋዊ ደስታ እንደ ጤዛ ጥዋት ታይቶ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከመጥፋቱም በላይ ፍጻሜውም በቀላሉ የማይገመት ሐዘንና ብስጭትን የሚያስከትልና መመለሻ የሌለው ሞት ነው ።

ንዕመናዊ ሶፋርም ይህንን አስመልክቶ ከጻድቁ ኢዮብ ጋር ሲናገር እንዲህ





www.ethiopianorthodox.org

ብሏል ። "የኃጢአተኛ ፋከራ እጭርመ ሆኑን የዘንጉዎችም ደስታ ቅጽበት መ ሆኑን አታውቅምን ? ሲል ከጠየቀ በኋ ላ ከፍታው ወደ ሰማይ ቢወጣ ራሱም እስከ ደመና ቢደርስ ለዘለዓለም ይጠፋ ል እንደ ሕልምም ይበራል ብሏል ኢዮ ፳ ፥ ፩

አሁንም ቢሆን ደስታው ጊዜያዊ ከ ሆነ ከሕልም ተነጥሎ የሚታይ ነገር አ ይደለም እንደሚታወቀው ሕልም የራ ቀውን አቅርቦ ያልተጨበጠውን አስ ጨብጦ በቅዠት መልክ ሲያሳይና የሆነ ውንና ያልሆነውን ነገር ሁሉ በሕልም መንፈስ ሲያስጎመጅ እውነት ይመስላ ል ኋላ ግን ይህንን ሁሉ ሲያዩ ቆይተው ከእንቅልፍ ሲነቁ ታይቶ የነበረውና በ የመልኩ እየታየ ሲያስጎመጅ የቆየው ወዴት እንደ ደረሰ የት እንደገባ የደረሰ በት ሳይታወቅ እንደ ጢስ በኖ ጠፍቶ ይቀራል እንደዚሁም ሁሉ ጊዜያዊ ደስ ታ ለጊዜው የልብን ደዌ የሚፈውስ ው ስጣዊ ሕሊናንም የሚያድስ ይመስላል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን እነዚያ በተድላ ና በደስታ ተውጠው የነበሩት ሰዎች ጊ ዜ ተለውጦባቸው ሲያዝኑና ሲያለቅ ሱ ይገኛሉ ሲያዝኑና ሲያለቅሱ የነበሩ ት ደግሞ ሐዘናቸውን ረስተው ብስጭ ታቸውንም አስወግደው በመንፈሳዊ ስ ሜት ሲደነቁ ይገኛሉ። የቤተ ክርስቲያ ን ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብም ስለዚሁ ሲናገ ርና ሥጋዊ ደስታ ስለሚያስከትለው ጠንቅ ሲገልጽ "በሌሊት ለከንቱ ነገር መትጋት እንደማይገባቸው ጠብቃቸ ው ይህች ውም ነፍስን የምታጠፋ ናት ካለም በኋላ የዚህን ውጤት ሲያብራራ ያንጊዜ ልቅሶ ይሆናል ግን የማይጠቅ ም ልቅሶ ነው ።

ያን ጊዜ ፍጻሜና ማኅለቅት እንደ ሌ ለው እንደ ክረምት ውኃ ዕንባ ይፈሳል ነጣቂ መብረቅና የሚያስደነግጥም የነ ጐድጓድ ቃል የሚቆርጥና የሚከፍል ብርቱ ብልጭልጭታ ወደ እነርሱ ይላ ካል ይኸውም የኃጥአን ዕድላቸው ነው ይላል ያዕ.ቅዳሴ ቁጥር ፹፯

እንግዲህ የሥጋዊ ተድላ ደስታ ው ጤት ይኸው ነው ሌላ ፍሬ ነገር የለው ም ጠቢቡ ሰሎሞን የተደላና የሥጋ ዊ ደስታ ፍጻሜ ሐዘንና ልቅሶ መሆኑን ሲገልጽ እንዲህ ሲል አመልክቷል በሳ ቅ ልብ ያዝናል የደስታም ፍጻሜ ልቅሶ ነው " ምሳ ፲፬ ፥ ፲፫

ሥጋዊ ደስታ የዚህ ዓይነት መልክ ሲኖረው መንፈሳዊ ደስታ ግን ከዚህ ለ የት ያለ ነው ይኸውም በመንፈሳዊ ተ ግባር የተሰበረ ልቡና ያላቸው ሰዎች ጊ ዜያዊ ደስታ ደስ አያሰኛቸውም ከዚህ ም የተነሣ ምድራዊውን ዓለም በሰማያ ዊ ዓለም ለውጠው የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ ንቀው በመንፈሳዊ ሥራ ሲደክ ሙ ይኖራሉ ።

ችግር ሲደርስባቸውም እንኳን በደረ ሰባቸው ችግር ሳያዝኑና ሳይለቀቁ አም ላካቸውን እያመሰገኑ ደስ ብሏቸው የ ሚኖሩ በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም "ለእኛ ከዚህ በእሸዋ የተሠራ ነፋሳት የሚነፍሱበት ፈሳሾች የሚገፉት ቤት ያለን አይደለም በላይ ያለች ነፃ የምታ ወጣ ኢየሩሳሌም (መንግሥተ ሰማያት) ናት እንጂ" ተብሎ እንደ ተጻፈ ሰማያ ዊውን ዐለም እጅ ለማድረግ ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን ከፍተኛው ን ተጋድሎ ሲፈጽሙ ይኖራሉ ። ይህም ለከንቱ አይደለም መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ለደቀመዛሙርቱ(ወትከውኑ ጽሉ እነ በእንተ ስምየ) "በእኔ ስላመናችሁ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ» ሲል ቀደ ም ብሎ የሰጣቸውን ማሳሰቢያ በተግ ባር ለመተርጐም ያልተቀበሉት ጽ ዋትወ መከራ አልነበረም ። ሐዋርያት ም ሁሉ የክርስቶስን አምላክነት ለመ መስከር ወንጌልንም በመላው ዓለም ለማዳረስ በምከሩበት ጊዜ ኢአማን ያን ቢያሰሯቸውና በልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ቢያስቃይዋቸውም እንኳ በፊታ ቸው ትንሽ የሐዘን ምልክት አይታይባ ቸውም ነበር እንዲያውም የሐዘን ምል ክት ከፊታቸው መታየቱ ቀርቶ ሲታሠ ሩና ሲከሰሱ ደስ ይላቸው እንደነበር ወ ንጌላዊው ሉቃስ ገልጾ ሲጽፍ (ወወጽ ኡ እምአውድ እንዘ ይትፌሥሑ እስመ ከፈሉሙ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ) ሐዋርያ ትን ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፏቸው በ ኢየሱስም ስም እንዳይናገሩአዝዘው ለ ቀቁዋቸውእነሱምስለስሙ ይናቁዘንድ የተገባቸው ሁነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎ ው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ ይላል የሐ ዋ ሥራ ፭ ፥ ፵፩

ሌሎችም የወንጌል መልእክተኞች ስለ ክርስቶስ በሚያስተምሩበት ወቅት ለምን ታስተምራላችሁ ተብለው እንደ አንድ ወንጀለኛ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት እየወሰዱ ቢያንገላትዋቸውው የወ ርቅ ካባ እንደ ተሸለሙና ታላቅ ጸጋ እ ንዳገኙ ይሰማቸው ነበር እንጂ ለምን- ለችግርና ለልዩ ልዩ ጽዋትወ መከራ ተ ጋለጥን እያሉ አያዝኑም ነበር ደስታቸ ውም ከዕለት ወደ ዕለት ይጨመርላቸ ው ነበር በሥራትም መንፈሳዊ ሥራ ም ነው በጨመርንበት ይላሉ ።

"እነሆ አምላክ መድኃኒቴ ነው ጌታ እግዚአብሔርም ኃይሌና ዝማሬየ ነው መድኃኒቴም ሁኗልና በእርሱ ታምኘ አልፈራም " የሚለውን የኢሳይያስን ቃል በማስታወስ በደስታ ይዋጣሉና ኢሳ ፲፪ ፥ ፪-፫

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶ ስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ " ስለ ክር ስቶስ በድካም በመንገላታት ፣ በችግር ም ፣ በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛ ል ብሏል 2ኛ ቆሮ ፲፪፥፲ እርግጥ መከራ ለጊዜው ደስ አያሰኝም ነገር ግን መከራውን ታግሠው ለተቀበ ሉት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ስለሚያፈራ ላቸው በመከራው እንጻር እጽፍ ድርብ ደስታ እንደሚጨምርላቸው አያጠራጥ ርም ። ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚሁ ሲና ገር " ቅጣት ለጊዜው የሚያሳዝን እን ጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅ ያፈራላቸዋል ብሏል ዕብ ፲፪ ፥ ፲፩ የሐዘን ውጤት መጨረሻው ደስታ መሆኑን የገለጹ እነ ጳውሎስ ብቻ አይደ ሉም፣ ከእነ ቅዱስ ጳውሎስ በፊት የነበ ሩትም ሰዎች በሰፊው ገልጸውታል ነ ቢዩ ዳዊት "በልቅሶ የሚዘምሩ በደስ

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህን [illegible] ግለ ሰቦ ችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከ[illegible] ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org